Wisdom at the source of the Blue Nile

እውነትን መፈለግና ስሲላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

# ናይል THE NILE



ኢ-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

ናይል 4ኛ ዓመት፣ ቁጥር 5፣ ጥቅምት 2009

## የምርምር ዩኒቨርሲቲ የመገንባት ጉዟችን በራዕይ ጥበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)

## What Does It Take To Be a Researcher?

Yinager Teklesellasie

## From Fault-Finding to Empowering: How Can We Build a More Learning-Centered Culture of Student Research at Bahir Dar University?

Vachel Miller
Haftu Hindeya
Ahmed Yibrie

## የማላታየን ቅኝት፡ ከባዮኬሚስትሪ የትምህርት ክፍለ ጊዜ እስከ የማሳ ላይ ድምጹ

መክሊት ጋርደው





*BDU's academic and adminstrative staffs at Renaissance Dam*





*Life Skill training for first year students of BDU*



*Humanities faculty launches the first issue of Ethiopian Journal of Language, Culture and Communication*

"ሴቶች ያመኑበትን ሥራ በፆታ የሥራ ውስንነት ሳያምኑ በፈቀዱት ሥራ በፈለጉት የሥራ መስክ በመሰማራት ጥሩ ውጤት ማምጣት ይኖርባቸዋል::"

ወ/ሮ ተስፋ ጌታሁን

ገጽ 8

## ውርስ (ልብ ወለዳዊ ወግ)

በደስታ ተከስተ

እውነትን መፈለግና ስሲላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

# Bahir Dar University

## Motto of Bahir Dar University

"Wisdom at the Source of the Blue Nile"

"ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ"

## Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

## Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

### Core Values

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility


# ናይል ጋዜጣ

በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ



**የአማካሪ ቦርድ አባላት**

ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
አቶ አብይ መንክር
አቶ እምቢያለ በየነ
ወ/ሮ ሰውነት አለሙ
አቶ በላይነህ ወርቁ
ዶ/ር አልማዝ ጊዜው
አቶ ቢሰማ ካሳ
ወ/ሮ መድኃኒት በላቸው
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

**ዋና አዘጋጅ፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሂሩት አድማሱ

**አርታኢዎች**
ሂሩት አድማሱ
የኑስ ኑሬ

**ግራፊክስና ሌይአውት፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ዘጋቢዎች፡-**
ታድዬ አስማረ
አምሳሉ ጥላሁን
ትዕግስት ዳዊት
ሙሉጎጃም አንዷለም

**አምደኞች፡-**
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ይናገር ተ/ስላሴ
ቫሄል ሚለር
ሀፍቱ ህንዳዬ
አህመድ ይብሬ
ደስታ ተከስተ
ታምሩ ከፈለኝ
ቤተልሄም ሃይለማርያም
መክሊት ጋረደው

**ፎቶ አንሺዎች፡-**
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

**የኮምፒውተር ጽሁፍ፡-**
የሻለም መንግስቴ
እስከዳር ይስማው
አቡኔ ደርሶ

**ትራንስፖርት፡-**
ማናለ ኃይሌ

**መልእክተኞች፡-**
ንብረት ታፈረ
አለምነሽ ሙሉ
መልሸው አጥናፉ



ስልክ፡- +251 583206088
+251 583207023

## ርዕሰ-አንቀጽ

# መማር ማስተማሩን ውጤታማ የማድረጉ ጉዞ በውጤት የማጀብ ጅምር ይቀጥል!

ያሳለፍነው 2008 ዓ.ም በርካታ ተማሪዎችን ያስተማረበት፣ ያስመረቀበትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ዓመቱን ያገባደደበት ወቅት ነበር - ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

በመማር ማስተማሩ ዘርፍ በልዩ ልዩ መርኃ ግብሮች በርካታ ተማሪዎችን በማሰልጠን፣ አዳዲስ መርኃ ግብሮችን በመክፈት ወደ አዲስ የከፍታ ማማ ላይ የወጣበት ወቅት ነበር፡፡ በተለይ ዩኒቨርሲቲው በድህረ - ምረቃ መርኃ ግብር ላይ የሰጠው ልዩ ትኩረትና በዚሁ አቅጣጫ ያከናወናቸው ተግባራት ያጠንክር ይቀጥልበት የሚያሰኙ ናቸው፡፡ ሀገር ተረካቢን ትውልድ በዕውቀትና በክህሎት አንፆ ለሀገር ግንባታው ርብርብ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንዲኖረው የማድረግ ወርቃማ ተልዕኮ የተሰጠው ዩኒቨርሲቲያችን የሀገር አለኝታነቱን በተግባር የለወጠ ተቋም ነው፡፡

የመማር ማስተማሩ ሥራን የሚያሳልጡ ለትምህርት ጥራትና በብዙኃኑ ላይ ውጤት ሊያመጡ የሚችሉ ለብቻ ከመሮጥ በጋራ በመንቀሳቀስ ይበጃል ከሚል መነሻ እየተተገበረ የሚገኘው ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት የማሰራቱ ተግባር ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ይህን አቅጣጫ በመተግበር ለበለጠ ስኬት መትጋቱን ይቀጥላል፡፡

የሞጁላራይዜሽን ትምህርት አሰጣጥ ሂደት በሁሉም ደረጃ እንደ የትምህርት መስኩ ሁኔታ በመተግበር ያሉበትን ጠንካራ ጎኖች አጠንክረን የሚሻሻሉትን በማሻሻል በጥራቱ ለውጥ በሚያስመዘግብበት ደረጃ በመተግበሩ ረገድ ያለውን አፈፃፀም የማሳደጉ ሥራን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

ለሀገር ልማትና ዕድገት ወሳኝ የሆኑ የትምህርት መስኮችን በመክፈቱ በከፍተኛ ደረጃ ያሉ ባለሙያዎች፣ ምሁራን እና ተመራማሪዎች የማፍራቱን ሥራ በተያዘው ዓመት በላቀ ደረጃ በመፈፀም ሰላማዊ መማር ማስተማር የሰፈነበት የትምህርት ዘመን ለማድረግ በቂ ዝግጅት ተደርጓል፡፡ በእያንዳንዱ ዕለት በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ የዩኒቨርሲቲው መካከለኛና ከፍተኛ አመራሮች እንዲሁም የአስተዳደር ቦርድ የቅርብ ድጋፍ ታክሎበት ዓመቱን በላቀ ውጤታማነት ለመፈፀም ርብርብ እየተደረገ ይገኛል፡፡

ዓመቱ ለአዲስ ገቢ ተማሪዎችም የተለያዩ የህይወት ክህሎታቸውን በሚያሳድጉ ሥራዎች ተጀምሯል፡፡ ዓመቱን በበለጠ ውጤታማነት ለመፈፀም እጅ ለእጅ ተያይዘን ለዩኒቨርሲቲያችን ውጤታማነት የምንተጋበት እንዲሆን የናይል ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ልባዊ ምኞታችን ለመግለፅ እንወዳለን!

**እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!**

**ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን**

በናይል ጋዜጣ ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 512 በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

## ቁልፍ መልዕክት

# የምርምር ዩኒቨርሲቲ የመገንባት ጉዟችን በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

የራዕይ ጥበብ 2017 ዋነኛ መገለጫ የምርምር ዩኒቨርሲቲ መመስረት ነው፡፡ በዚህም መሠረት ምርምርን ማሳለጥ የሁሉም ስራችን ኮምፓስ እንዲሆን በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ከሁሉም በላይ ለምርምር ልዩ ትኩረት የሚሰጡ አመራሮች፣ መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞችና ተማሪዎች ለመፍጠር አሁንም በርካታ ስራ መስራት ይጠይቀናል፡፡ በዚህ አጭር ጽሑፍ ከምርምር ስራችን ጋር በተያያዘ በቀን ተቀን ተግባራችን መገለጫ የሆኑትን ስራዎች በማንሳት የሚቀሩንን ጉዳዮች ለማመላከት እሞክራለሁ፡፡

የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለድህረ ምረቃ መርኃ ግብር /ፕሮግራም/ ልዩ ትኩረት የሚሰጥና ለሁሉም ስራዎቹ እንብርት አድርጎ ያያል፡፡ በዚህም መሠረት በድህረ ምረቃ መርኃ ግብር ለሚሳተፉ ተማሪዎችና መምህራን የሚፈልጓቸውን ግብዓት የማሟላት ስራ ዋነኛ ስራ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የቢሮ፣ የዘመናዊ መረጃ አቅርቦት፣ ተስማሚና በሚገባ የተደራጁ ቤተ-ሙከራዎች እና ቤተ-መጽሀፍት፣ መማሪያ ክፍሎችና መኖሪያ ቤቶችን ባካተተ መልኩ ግብዓት ለማሟላት በተጠናከረ መልኩ ይሰራል፡፡ በዚህ ዕይታ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ረጅም ርቀት መጓዙ እንደተጠበቀ ሆኖ አሁንም ያሉብን ክፍተቶች ብዙ ናቸው፡፡ ትልቁና ዋነኛው ችግራችን የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመመስረት ከሚሰሩ ስራዎች ዋነኛው የድህረ ምረቃ መርኃ ግብሮችን ማስፋፋትና ማጠናከር መሆኑን ተገንዝበው ለስኬቱ የሚቻለንን ሁሉ ማድረግ አለብን ብለው በአመለካከት የተለወጡ አመራሮች፣ መምህራን፣ የድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችና ተማሪዎች ቁጥር በሚፈለገው ደረጃ አለመሆኑ ነው፡፡ ይህም ምርምር ላይ ማተኮራችን የቅድመ ምረቃ መርኃ ግብሩን መማር ማስተማር የሚጎዳ የሚመስላቸውና የሚያዳክም የሚመስላቸው ከሁሉም የማህበረሰባችን ክፍል መኖራቸው ነው፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት ጠንካራ የተግባቦት ስርዓትን መዘርጋትና የውይይት መድረኮችን በመፍጠር መፍታት ይጠበቅብናል፡፡ በመሰረቱ ምርምር የማይሰራ/የማትሰራ መምህር ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት እጅግ ያዳግተዋል/ታታል፡፡ መምህራኖቻችንን ምርምር እንዲሰሩ ባደረግናቸው ቁጥር ጥራት ያለው ትምህርት የማረጋገጥ ተግባራችንን በብዙ ርቀት እንደወሰድነው መገንዘብ ጠቃሚ ነው፡፡ መምህራኖቻችን ደግሞ ሊመራመሩ የሚችሉት እንዲሁ በግላቸው ሳይሆን ከሚያማክሯቸው የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ጋር በመሆን ተማሪዎቹ መረጃውን የመሰብሰብንና የመጀመሪያ ደረጃ ትንተና ለመምህራቸው እያቀረቡ የመምህራቸውን አስተያየት ተጨምሮበት ለህትመት ሲበቃ ነው፡፡ ለዚህ ነው የምርምር ዩኒቨርሲቲ ዋነኛ የምርምር የስበት ማዕከል ድህረ ምረቃ መርኃ ግብሮች የምንለው፡፡

በዋነኛነት የጠቀስነው የአመለካከት ችግር የሚወልዳቸው በርካታ የአፈፃፀም ችግሮችም አሉ፡፡ በድህረ ምረቃ መርኃ ግብሮች የሚሳተፉ መምህራንና ተማሪዎች የሚፈልጓቸውን ግብዓቶች በወቅቱ አለማሟላትን ጨምሮ ፕሮግራሞች እንዲሁ የተተዉ የሚመስልበት ድረስ ክፍተት አለ፡፡

በአሁኑ ወቅት በሁሉም ዘርፎች የምንሰራ የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብ የምንኖረውና የምንሰራ ለተወሰነ ጊዜ ነው፡፡ በታሪክ አጋጣሚ ከትውልድ ትውልድ በሚተላለፍና ለረጅም ዘመን በሚቆይ ተቋም የመስራት ዕድሉን አግኝተናል፡፡ ይህን እጅግ ወርቃማ አጋጣሚ ተጠቅመን የራሳችንን የማይሞት አሻራ የማስቀመጥ ዕድል ልንጠቀምበት ይገባል፡፡ የድህረ ምረቃ መርኃ ግብሮቻችን ትናንሽ አበቦቻችን ናቸው፡፡ እነዚህን አበቦች በሚገባ ተንከባክበንና አስፋፍተን በተከታታይ ፍሬ በሚያፈሩበት መሰረት የመስራት ተልዕኮ የተሰጠን ትውልዶች ስለሆንን ስራችንን በሚገባ ተወጥተን ተከታታይ ትውልዶች ቀጣይ ደረጃዎችን የሚሰሩ እንጅ እኛ ያልሠራነውን የሚሰሩ እንዳናደርጋቸው በትጋት መስራት ጠቃሚ ነው፡፡

ለራዕይ ጥበብ 2017 ስኬት

**To follow the latest news about BDU, check out our website:**
**www.bdu.edu.et**
**facebook page:**
**www.facebook.com/bduethiopia**

# አበይት ዜናዎች

## ለመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች የህይወት ክህሎት ስልጠና ተሰጠ

በሙሉጎጃም አንዷለም

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስርዓተ ጾታ ጽ/ቤት አዘጋጅነት በ2009 ዓ.ም ለገቡ አዲስ መደበኛ ተማሪዎች ለሁለት ተከታታይ ቀናት የህይወት ክህሎት ስልጠና በሁሉም ግቢዎች በመምህራን ተሰጠ፡፡

የጽ/ቤቱ ዳይሬክተር ዶ/ር አልማዝ ጊዜው የስልጠናው ዋና ዓላማ ለሁሉም የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች የሚሰጠው ስልጠና አካባቢያቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ለቀው ከተለያየ ቦታ የመጡ በመሆናቸው በግቢ ውስጥና በውጭ የተለያዩ ችግሮች ሲያጋጥማቸው ችግሮቹን አስቀድመው እንዲያውቁትና እንዴት መቋቋም እንደሚችሉ እንዲሁም በዩኒቨርስቲው ቆይታቸው በትምህርታቸው ውጤታማ ሆነው እንዲወጡ ብሎም ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ለማጠንከር ነው ብለዋል፡፡

ስልጠናው አዲስ ተማሪዎች ራሳቸውን አውቀው የሚያጋጥማቸውን ችግሮች እንዴት መፍታት እንዳለባቸው፣ ከሰዎች ጋር ያላቸውን ተግባቦት ማጠንከር፣ የአቻ ግፊትን እንዴት መቋቋምና ማስወገድ እንዳለባቸው፣ በዕቅድ የመመራት ባህልን ማዳበር፣ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም፣ የጾታ ትንኮሳን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል፣ ጭንቀትን ባስወገድና የቤተሰብ ናፍቆትን እንዴት መቋቋም እንደሚችሉ፣ የቡድን ሥራንና የመረዳዳት ባህልን ማዳበር፣ ውጤታማ የሆነ የማንበብ፣ የማስታወሻ አያያዝ፣ በክፍል ውስጥ የማቅረብ እንዲሁም የፈተና አወሳሰድ ስልቶች ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የስልጠናው ተሳታፊዎች እንደገለጹት አካባቢያቸውን ለቀው ሲመጡ የተለያዩ ችግሮች እንደሚያጋጥሟቸው ስጋት ቢኖርባቸውም ከስልጠናው የተለያዩ ክህሎቶችን በመረዳት በራስ የመተማመን ብቃታቸውን ለማዳበርና ውጤታማ ሆነው ከዩኒቨርሲቲ እንዴት መውጣት እንዳለባቸው ግንዛቤ ማግኘታቸውን ተናግረዋል፡፡

## የትምህርት ምርምርን ከተግባርና ፖሊሲ ጋር ለማቀናጀት የምክክር መድረክ ተካሄደ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የፔዳጎጂና ትምህርት ምርምር ተቋም አስተባባሪነት "ርምጃችንን እንጀምር፣ ምርምርና ተግባርን እናቀናጅ" በሚል ርዕስ ከባለድርሻ አካላት ጋር በዩኒቨርሲቲው ፔዳ ግቢ የምክክር መድረክ ተካሄደ፡፡
የተቋሙ ዳይሬክተር ዶ/ር ዳዊት አስራት እንደተናገሩት የምክክር መድረኩ አላማ የትምህርት ምርምር ስራን እንዴት ከተግባርና ከፖሊሲ ጋር ማቀናጀት እንደሚገባ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት በማካሄድ የወደፊት አቅጣጫዎችን በጋራ ለመተለም ነው፡፡ የትምህርት ስርዓቱን የሚያስተዳድረው አካልና በትምህርት ላይ ምርምር የሚሰራው አካል ተነጣጥለው መሄድ እንደሌለባቸውና አብዛኛው ምርምሮች ከግል ፍላጎት በመነጩ ጉዳዮች ላይ ሳይሆን በተግባር በትምህርት ቤቶች አካባቢ የሚታዩ ጉዳዮችን መሠረት ያደረጉ ቢሆኑ፣ ፖሊሲዎችና መመሪያዎችም ሃገራዊ አውድን ከግምት ውስጥ ባላስገቡ የውጭ መልካም ተሞክሮዎች ላይ ተመርኩዘው ከሚታቀዱ ይልቅ በተመራማሪዎቻችን የተገኙ ውጤቶችን መሠረት ያደረጉ ቢሆኑ እንዲሁም በትምህርት ምርምር፣ ተግባርና ፖሊሲ መካከል የሚኖረው ቅንጅት የተሻለ እንዲሆን አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለዋል፡፡
የምክክር መድረኩን የመሩት በአሜሪካ ኒውዮርክ ከተማ ውስጥ ከሚገኘው ሚዳሌ ኮሌጅ ስኩል ኦፍ ኢጁኬሽን የመጡት ዶ/ር በለጠ ከበደ ሲሆኑ የትምህርት ምርምር ከተግባርና ከፖሊሲ ጋር መቀናጀቱ የሚኖረውን ፋይዳና የሚቀናጅባቸውን መንገዶች የጠቆሙ ሲሆን ተሳታፊዎችም እነዚህ መንገዶች በሀገር ውስጥ ሊተገበሩ በሚችሉባቸው መንገዶች ላይ ሰፊ ውይይት አድርገዋል፡፡
በምክክር መድረኩ ላይ የትምህርትና ስነ ባህሪይ ኮሌጅ ምሁራን፣ የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ የባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ ጽ/ቤትና በባሕር ዳር ከተማ የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ባለሙያዎች ተገኝተዋል፡፡

## ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ የምርምር ጆርናል አስመረቀ

በትዕግስት ዳዊት

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ Ethiopian Journal of Language, culture and communication የተሰኘውን የምርምር ጆርናል አስመረቀ፡፡ የዩኒቨርሲቲው የድህረ ምረቃ ዲን ዶ/ር አለማየሁ ቢሻው በምርቃቱ ላይ በመገኘት ጆርናሉን ይፋ አድርገዋል፡፡

የሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ ዲን ዶ/ር ዳዊት አሞኜ በምርቃቱ ላይ እንደተናገሩት ጆርናሉን ለሕትመት ለማብቃት ብዙ ውጣ ውረዶች እንደነበሩ ገልጸው ጆርናሉ በቋንቋ፣ በባሕል፣ በስነ ጽሁፍ፣ ስነ ልሳን፣ መገናኛ ብዙኃን፣ ጋዜጠኝነትና ተግባቦት እንዲሁም ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የጆርናሉ አማካሪ ቦርድ አባልና የዩኒቨርሲቲ ምሁር ፕሮፌሰር ዓቢይ ይግዛው ዩኒቨርሲቲው የሶስተኛ ዲግሪ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ በመሆኑ ጆርናሉ እንደመረጃ እና ማጣቀሻ ስለሚያገለግል ወደፊት የመረጃ እጥረት ስለማይኖር በአመት ከሁለት ጊዜ በላይ ለማሳተም የፋኩልቲው ምሁራን የበኩላቸውን መወጣት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

ህትመቱን ለማሳተም ከሁለት ዓመታት የፈጀ ሲሆን ጆርናሉን እውን እንዲሆን የፋኩልቲው ምሁራንና ሌሎች አካላት አስተዋፅኦ እንደነበራቸው ተገልጿል፡፡ በቀጣይም ህትመቱን ለማስቀጠልና ለማሻሻል እንዲሁም አለም አቀፋዊ ተቀባይነቱን ለማሳደግ ሁሉም መምህራንና ተመራማሪዎች የራሳቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ ቀርቧል፡፡

# ዜና ትንታኔ

## በምርምር በመታገዝ የአፈር ክለትን መቀነስ እንደሚቻል ተገለፀ

በአምሳሉ ጥላሁን እና በሙሉጎጃም አንዱአለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የሲቪልና ውሃ ኃብት ምህንድስና ፋኩልቲ 'የአፈር ክለትን ለመቀነስ ቦረቦርን ማዳን' በሚል መሪ ቃል የመስክ ጉብኝትና የምክክር መድረክ በምዕራብ ጐጃም ዞን ዋና ከተማ ፍኖተ ሰላም አካሄደ፡፡

በምክክር መድረኩ መክፈቻ ላይ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የሲቪልና ውሃ ኃብት ምህንድስና ፋኩልቲ መምህርና ተመራማሪ እንዲሁም የፒር (PEER) ሳይንስ ፕሮጀክት አስተባባሪ ዶ/ር ሰይፉ አድማሱ ፕሮጀክቱ ከአራት ዓመት በፊት በአሜሪካ ህዝብ ተራዶ ድርጅት የገንዘብ ድጋፍ እንደተጀመረ እና ከጥናት ሥራዎቹም አንዱ የቦረቦር የአፈር ክለት መንስኤዎችን እና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በመለየት በደብረ መዊ እና በቋራ እንጭላላ ቀበሌዎች ላይ ስራ እንደጀመረ እና ለውጥ እንደተገኘባቸው ገልጸዋል፡፡ ስራው ሲጀመር የአካባቢው ማህበረሰብ የአመለካከት ችግር እንደነበረና ፕሮቹን ሰብሮ ለመግባት ብዙ ጊዜ እደፈጀባቸው ገልጸው ነገር ግን ግንዛቤ መፍጠር ላይ ትኩረት ተሰጥቶ በመሰራቱ ማህበረሰቡን በብዙ መልኩ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል ብለዋል፡ ፡ ዶ/ር ሰይፉ አክለውም እንደተናገሩት ዩኒቨርስቲው የ3ኛ ዲግሪ ትምህርትን እያስፋፋ እንደሆነ እና ተመራማሪዎችም በምርምር ስራው የነቃ ተሳትፎ እያደረጉ እንደሆነ ጠቁመው የፋኩልቲው ተማሪዎች በደብረ መዊ እና በቋራ እንጭላላ ቀበሌዎች ላይ እያካሄዱት ያለው የምርምር ስራ አንዱ ማሳያ ነው፡፡

በሀገራችን ላይ ሰማንያ በመቶ በላይ የሚሆነው ህዝብ የሚተዳደረው በግብርና በመሆኑ በመንግስት በኩል ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ለውጥ ያመጡ የተፈጥሮ ኃብት ልማት ሥራን ህብረተሰቡን በማንቀሳቀስ እየተሰራ መሆኑን የተናገሩት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በግብርና ቢሮ የተፈጥሮ ልማት እና ጥበቃ የሥራ ሂደት ባለቤት አቶ ጌታቸው እንግዳአየሁ ናቸው፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሰብል እና በእንስሳት ኃብት ላይ ብዙ ሥራዎችን እየሰራ እንደሆነ የተናገሩት አቶ ጌታቸው በተፈጥሮ ኃብት ሥራው ግን ጅምር እንደሆነ ጠቁመው አንድ ሀገር የሚያድገው በምርምር በተደገፈ ዕውቀት በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው በእነዚህ ዘርፎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራባቸው አሳስበዋል፡፡

በምክክር መድረኩ ላይ ዶ/ር ሰይፉ አድማሱ እና በዶ/ር አሰፋ ደርብ እንዲሁም የ3ኛ ዲግሪ ተማሪዎች በሆኑት ደሳለኝ ጫኔ እና መሰረት በላቸው በደብረ መዊ እና በቋሪት እንጭላላ ቀበሌ የአፈር ክለት መንስኤዎችና ለመቀነስ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ላይ የተሰሩ ሥራዎችን አቅርበው ውይይት ተደርጐባቸዋል፡፡

ከምዕራብ ጐጃም፣ አዊ፣ ምስራቅ ጐጃም፣ ደቡብ ጐንደር፣ ከሰሜን ጐንደር ዞኖች፣ ከግብርና ቢሮ እንዲሁም ከጎንደር፣ ደብረ ታቦር እና ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡት ባለሙያዎች በቋሪት እንጭላላ ቀበሌ ጉብኝት ያካሄዱ ሲሆን ፋኩልቲው በተግባር የሰራቸው ስራዎች በጣም አበረታች እንደሆነ እና ልምድ እንደቀሰሙበት ከጉብኝቱ በኋላ በተደረገው ውይይት ላይ ገልፀዋል፡፡

በአካባቢያቸው የተከሰተው የቦረቦር ወይም የአፈር ክለት የሰው ልጅ በሚሰራው ሥራ ችግር የሚከሰት ሳይሆን በእግዚአብሄር ቁጣ እንደመጣባቸው ያምኑ እንደነበር እና የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሮጀክት በአካባቢያቸው የተለያዩ የግንዛቤ ሥራዎችን ሲሰራ ማህበረሰቡ ስጋት እንደነበረው የገለጹት የቋሪት እንጭላላ ቀበሌ ኗሪ የሆኑት አቶ ችሎት ሞሴ የሰው ልጅ ይህን ትልቅ የቦረቦር ቦታን እርከን ሰርቶ ያቆመዋል የሚል ሀሳብ እንዳልነበራቸውና ይልቅስ ይህ ፕሮጀክት መሬታችንን ሊወስድ ነው የሚል ስጋት እንደነበራቸው አስታውሰዋል፡፡ በተደጋጋሚ የተሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ግን በማህበረሰቡ በኩል ትልቅ ግንዛቤ እንደፈጠረና እና በዚህ አምስት ዓመታት ውስጥ የተሰራው ሥራ የአካባቢውን ህብረተሰብ ተጠቃሚ እንዳደረገ አቶ ችሎት ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ፋኩልቲው ከዚህ በፊት የፒር ሳይንስ ኘሮጀክት በፍኖተ ሰላም ከተማ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት መድረክ ያካሄደ ሲሆን በቋሪት ወረዳ እንጭላላ ቀበሌ የመስክ ጉብኝት አካሂዷል፡፡ የኘሮጀክቱ አስተባባሪ ዶ/ር ሰይፉ አድማሱ የጉብኝቱንና የውይይቱን ዋና ዓላማ እንደገለጹት ፋኩልቲው ከሚያካሂዳቸው በተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ዘርፍ የተለያዩ ጥናቶችን አንዱ የቦረቦር የአፈር ክለት መነሻ መንስኤዎች፣ ምክንያቶች፣ አቅጣጫዎችና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን መለየት በመሆኑ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ከከፍተኛ ደረጃ የቦረቦር ተጋላጭ በሆነው የእንጭላላ ተፋሰስ ቦታዎችና ሌሎች ተዛማጅ ስፍራዎች ላይ በረቦር የሚያደርሰውን ጉዳት እንዴት ማዳን እንደሚቻል በምርምር የተካሄዱ ተግባር ተኮር ስራዎች እና በጥናት የተገኙትን ውጤቶች ለልማት ጣቢያ ባለሙያዎችና ለአርሶ አደሮች ግንዛቤ ለመፍጠር እንዲሁም የታዩ ተግዳሮቶችን ለይቶ ለማውጣት ታልሞ ነው፡፡



ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# What Does It Take To Be A Researcher?

**By Yinager Teklesellasie,**
**Department of English Language and Literature**

How many research articles can you publish in one academic year? If you publish even one research article in a single academic year by working individually, then you should be proud of yourself. In 2013, I published a research article and it took me four months before I sent it to the journal which published my article. I am usually surprised and even suspicious when I hear that some of our colleagues are able to publish up to fifteen research articles in one academic year. As far as I know, Bahir Dar University does not have a single full-time researcher. Everyone teaching at BDU is employed as a lecturer; therefore, every member of the academic staff is a full-time teacher. If you are hard working and if there is good funding for doing research you can do research in addition to your main responsibility, which is teaching. However, if you like teaching and spend much time for preparing yourself for your classes and spend as much time grading your students' assignments, then doing research even with the provision of good funding can be very challenging.

So how is it that our colleagues who are full-time teachers like us are able to publish ten or more research articles in one academic year, when more than 95% of us are unable to publish even a single research article? How can anyone publish on average more than one research article every month in addition to teaching full time? There must be some secret. Just imagine the time and effort you need to do research and publish its results. You start the research process by writing a proposal which you usually have to defend before getting any funding. Reviewing the literature requires several weeks or months. You may have to develop your data gathering instruments before collecting data for your research. The process is long and I don't have the space or the intention to write about every step in the process. The point I am trying to make is clear – you need months to finish a research project and publish it in a journal. So how did some of our colleagues succeed in publishing ten or more research articles in one academic year?

There could be many reasons. On of the possible reasons might be because these people are very hardworking and intelligent people. I have a lot of respect for anyone who is able to do and publish even a single research article in a year individually or in collaboration with colleagues. My fear and suspicion is that some of our colleagues just turn their students' research papers, which their students have done as a requirement for graduation, to a journal article and publish it as a co-author. Does turning your students' research papers into journal articles and publishing them as a co-author make you a researcher? I understand that this can be controversial and I remember having an informal debate with my colleagues about it a couple of years ago. As there were some colleagues who were in support of this practice, there were as many who thought that it was unethical. In my opinion, turning your students' research papers into a journal article and publishing it as a co-author is way different from doing your own research. When you turn your students' research papers into a journal article, you don't need to go out of your office. Everything is done for you by your students. The only thing you need to do is to read what they write and guide them through by writing a few comments and feedback. I would like to remind you that more often than not we teachers are paid for the advising or supervising we do. So do you think it is morally acceptable to claim your students' research work as your own? Can we really call these kinds of teachers researchers?

> ***In many universities, professors involve their postgraduate students in their research projects and go as far as giving their students the right to co-authorship.***

I think the university should have clear policies about research and publication. One of the policies should be requiring teachers to disclose the research project they are working on to research and publication coordinators and that the project should be their own. In many universities, professors involve their postgraduate students in their research projects and go as far as giving their students the right to co-authorship. The main objective of this scheme is to give postgraduate students practical experience in doing research. However, this is very different from the practice of changing one's advisee's research project into a research article and claiming co-authorship.

Once someone who was living in my neighborhood and was an extension postgraduate student of BDU asked me why it was important for his adviser to change his M.A. thesis into a research article. I told him the truth that if the article was published his adviser could get promoted. I am not exactly sure if it was revealed to this postgraduate student by his adviser that the student had the right to co-authorship if the article was published, but I doubt it very much. Professorship should be the result of hard work and not of sleaze. The university should acknowledge only those who epitomize dedication and integrity.

## በምርምር በመታገዝ የአፈር ...

ከገጽ 4 የዞረ

የተካሄደውን ውይይት የከፈቱት የጃቢጠናን ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ወለላው አማረ ሲሆኑ የምክክር መድረኩን ላዘጋጀው ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ምስጋና አቅርበው ተሣታፊዎች ከተለዩ ወረዳዎች የተውጣጡ በመሆናቸው የስልጠናው ተደራሽነት ሠፊ እንደሚሆን አስገንዝበው ተሣታፊዎች ያገኙትን ክህሎት በሚኖሩበት አካባቢ ተግባራዊ እንዲያደርጉ በአደራ መልክ አሳስበዋል፡፡ በመንግስት በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት ቦረቦርን የማዳን ስራ በአካባቢው በስፋት እየተሠራ መሆኑን የገለጹት አቶ ወለላው ከክልል እስከ ወረዳ ብሎም እስከ ቀበሌ ስራው ተስፋፍቶ እንዲቀጥል በተመረጠው ቦታ ላይ ሣይንሣዊ በሆነ መልኩ መሟላት ያለበትን ነገር ለሚመለከተው አካል በማሣወቅና የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን በመቋቋም ስራው ተጠናክሮ እንዲቀጥል አስገንዝበዋል፡፡

በውይይቱ ወቅት የእነጭላላን ተፋሰስ ጨምሮ በተለያዩ ቦታዎች የተከናወኑትን የቦረቦር ማዳን ስራዎች ለአርሶ አደሮች ግልፅ በሆነ አቀራረብ ተመራማሪዎች በምስል የተደገፉ በርካታ ጥናታዊ ፅሁፎችን አቅርበዋል፡፡ ቦረቦሮች ከማሳ ከሚከላ የአፈር መጠን ከሶስት እጥፍ በላይ እንደሚደርስና በአመት ከ1400 ብር በላይ በሄክታር እያንዳንዱ አርሶ አደር እንደሚያጣ የቀረቡት ፅሁፎች አመላክተዋል፡፡ ዝቅተኛ ተዳፋትነት ባላቸው መሬቶች ላይ የሚፈጠሩ ቦረቦሮችን በማዳን መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ደለልን ማስቀረት፣ የተፋሰሶቹ ግርጌ ማሳዎች ላይ እርከን ከመስራት መፋሰሻ ቦዮችን በመስራት ውሃን ከማሳ ማስወገድ፣ ጥልቀታቸዉ ዝቅተኛ የሆኑ ቦረቦሮችን በቅድሚያ በማዳን /በመከላከል/ ትላልቅ ቦረቦሮችን እንዳይፈጠሩ ማድረግ፣ የቦረቦር አናት እድገትን ለመቀነስ የቦረቦር ክፍል የሆነውን አናቱን በማንጋለል እና የድንጋይ ርብራብ በመስራት ማስቆም እንደሚቻል የጥናት ጽሁፎቹ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት ግብርና ቢሮ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሙያተኛ አቶ ገደፋው በየነን ጨምሮ ተመራማሪዎች እንዲሁም ከተለየዩ ወረዳዎች የተውጣጡ የልማት ጣቢያ ባለሙያዎችንና አርሶ አደሮች የተሳተፉ ሲሆን በምርምር የተደገፉ የቦረቦር ማዳን ስራዎችን ተጎብኝተው ሰፊ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ለቦረቦር የተጋለጠን ቦታ ለማዳን ከሚሠሩ ስራዎች አንዱ የሆነውን የቦረቦር አናትን ማንጋለል እና የድንጋይ ርብራብ አሰራር ዘዴ ስራ ሁሉም ተሣታፊዎች በተግባር አከናውኗል፡፡ በጉብኝቱ ወቅት ቦረቦርን ለማዳን የተሰራው ሠፊ ስራ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ በአካባቢው ከሚኖሩ አርሶ አደሮች ገለፃና በስራው ላይ ከተሰማሩ ተመራማሪዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ የወጭ ቆጣቢ የቦረቦር ማዳን ስራ ዝቅተኛ ጥልቀት ባላቸው እና የእድገት ደረጃቸው አናሳ የሆኑ ቦረቦሮችን በማዳን የአፈር መሸርሸርን በመቀነስ ውጤታማ እንሁን የሚል የጽሁፉ መልዕክት ለተሳታፊዎች ተሰራጭቷል፡፡

ተሣታፊዎች ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከመማር ማስተማሩ ባሻገር በምርምሩ ዘርፍ ወደ አርሶ አደሩ ወርዶ ችግር ፈች ምርምር በማካሄድ በተጨባጭ ያለውን ችግር በማየታቸው እንደተደሰቱ ገልፀው ለወደፊትም በሌሎች በቦታዎች ተደራሽነቱ እንዲስፋፋ ጠይቀው ለዩኒቨርሲቲው ያላቸውን አክብሮትና ምስጋና አቅርበዋል፡፡

# ውርስ (ልብ ወለዳዊ ወግ)

በደስታ ተከስተ
ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፀጥታ አገልግሎት

እድሜና ልምድ አብረው እንዳስተማሩኝ ከሆነ ወግ ከመጀመር በፊት ባህልና ጨዋነት የሚያመላክተውን አክብሮታዊ ሰላምታ ማስቀደም አለብኝና ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን ሰላማችሁ በጥፍ ይብዛ በማለት እቀጥላለሁ፡፡

የሰው ልጅ የዚህችን አለም የህይወት ዘመኑን አጠናቆ በሞት ከተሰናበተ በኂላ በነገር መካከል ስሙ ሊጠቀስ ከተፈለገ “ነፍሱን ይማረውና እገሌ” ይባላል፡፡ ነፍሱን ይማረውና...እየተባለ መነገሩ እንደኔ ባይመቸኝም የማህበረሰባችን ወግና ልማድ ነው፡፡

እንግዲህ መቼም የማህበረሰባችንን ልማድና ወግ አፈረስክ ተብዬ እዳልኮነን እኔም ለዛሬው ብቻ ይህን አባባል እጠቀምበታለሁ፡፡ነፍሱን ይማረውና ቅድመ አያቴ በህይወት በነበረበት ዘመን ከእኔ ጋር የነበረን... ቅርርቦሽ... በቃላት ተገልፆ የሚዘለቅ አልነበረም፡፡

ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው እራሴን እንደ እድለኛ እቆጥራለሁ እድለኛና ደስተኛም ነኝ... የደስታዬ ምንጭ ደግሞ አንዳንዱ ሰው (በተለይ በዚህ ዘመን) የአባቱን ስም ጠርቶ የአያቱን የማይደግም ባለበት እኔ ግን ከአያትም አልፌ ቅድም - አያቴን ከስም ያለፈ በአካልም ስለደረስኩበት ጠንቅቄ በማወቄ ኩራትም ጭምር ይሰማኛል “ከሞቱት ዘመዶችህ መካከል ለአንድ ቀን ያህል ማን ይነሳልህ; ተብዬ ብጠየቅ... ያለ ምንም ማመንታት ቅድመ አያቴን መላክ ጥበብን ነው፡፡

ከቅድመ አያቴ ጋር በነበርኩባቸው የልጅነት ጊዜአት እርሱ የነገረኝ ተረቶችና የሚያዜምልኝ ዘፈኖች ዛሬም ድረስ በልቦናዬ ውስጥ ተሰንቅረው በአምሮዬ እየታወሱኝ በኀሳቤና በትዝታ መንፈስ ያሽከረክሩኛል፡፡

መላከ ጥበብ ማለት በመንደሩና በአካባቢው የታወቀ ጨዋና ሰው አክባሪ እንዲሁም በዘመኑ የቀለም ቀንድ የሚባል ሀገር ወዳድ እንደነበረ አስታውሳለሁ፡ ፡ ታታሪም ሰራተኛ ነበር፡፡ በእርጅና ዘመኑ ደክሞት እቤት ከዋለም በኂላ ቢሆን ሥራ አልፈታም፡፡ የአካባቢውን ልጆች ሰብስቦ ፊደል በማስቆጠርና ሀገራዊ ታሪኮችን በመንገር እንዲሁም ተረት በማውራትና የዘፈን እንጉርጉሮ ሲያዜም ጊዜውን ያሳልፍ ነበር፡፡

በተለይም ድሮስ ቀን አይመሽ በዘይቤ ካልሆነ ሲመሽ የእርሱን ተረቶችና እጉርጉሮ ለመስማት የቤተዘመዱ ልጆች ምድጃውን ከበን ነበር የምናመሸው....

ያው ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት “ነፍሱን ይማረውና” ቅድመ አያቴ ካሉት ልጆች ሁሉ እኔን አብልጦ ስለሚወደኝ “ልጄ ተስፋ አለም ናማ... እስቲ ጀርባዬን ስለበላኝ እከክልኝ” ይለኝ ነበር እርሱ በሞት እስከተለየበት ቀን ድረስ የኔ ትልቁ ስራዬ የነበረው ማታ ማታ የእርሱን ወገብ ማሸትና የምድጃውን እሳት መቆስቆስ ነበር፡፡ ለዚህ ስራዬ የሚከፈለኝ ደሞዝ... ምግብ ሲመገብ ጠቀም ያለ ጉርሻ... ያጐርሰኝና አልጋውላይ ተኝቶ እንቅልፍ እስኪወስደው ድረስ የምርቃት ዶፍ ያወርድልኝ ነበር፡፡ ወዳጆቼ... ከእርሱ የሰማኂቸውን ተረቶች አሁን ለእናንተ ልገልፅላችሁ ብሞክር ጊዜ ስለማይበቃኝ ቀድመህ እኮ ስለሳቢነቱ አጨኸን ደግሞ ተረት አይሰለችም ውድ አንባቢዎቼን በጥቅሉ ቅድመ አያቴ ጥሩ የተረት አስተማሪ ነበር በማለት አልፋለሁ፡፡ በእርግጥ ሴት አያቴም ብትሆን በተረት በኩል አትታማም ከቅድመ አያቴ ተረቶች የእርሷ ተረቶች የሚለዩት በይዘታቸው ነው፡፡ ተረቶቿ ሁሉ የሚያተኩሩት” በድሮ ጊዜ... ከሚል ሀሳብ ተነስታ... ስለነ ጦጢትና አንበሳ ስለ አህያና ጅብ...ታሪክ ሲሆን በዘመኑ የአስፈሪነት ይዘት ያለው ተረቷ ደግሞ ስለ ጭራቅ የምታወራን ነው፡፡ አያቴ ተረቶቿን አውርታ ስትጨርስ “ልጆቼ... ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ” ትለናለች... እኛ ግን የዳቦ ነገር ስለማይሆንልን አያታችን አፍ ከማበስ ይልቅ... የእኛን ሆድ እምንሞላበት ነበር፡፡ አያታችን አውርታ ስትጨርስ እኛም የቻልነውን ያህል ተረት የማውራት እድሉን ትሰጠን ነበር፡፡

ቅድመ አያታችን ግን ተረቶችን አውርቶ ሲጨርስ፣ ‹‹ልጆቼ እደጉ ተመንደጉ... ሰሚ ጆሮ አስተዋይ ልብ ይስጣችሁ... ለወገን የምትበጁ ለሀገር የምትጠቅሙ ያድርጋችሁ... ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ፡ ፡ የአባይን ወንዝ ለኢትዮጵያ ምድር የፈጠረ እግዚአብሔር ይባርካችሁ...» ብሎ ነበር ንግግሩን የሚያቆመው፡፡

ውድ አንባቢዎች እስቲ እንደው የወጌ አስኳል የሆነውን የአባይ ወንዝና የቅድመ አያቴን ቁርኝት ጉዳይ ማውጋት ልቀጥል... ቅድመ አያቴ እንጉርጉሮ ከጀመረ... ግጥሞቹ ሁሉ አባይ... አባይ... የሚሉ ናቸው... እኔ ከማስታውሳቸው መካከል እንኳን ብጠቀስ...

“ ውሃ ወርዶ ወርዶ ማረፊያው አባይ

እናት ወልዳ ወልዳ ለሰው አገልጋይ፡፡

“ አባይ ውሃ ሞልቶ ይፈሳል ቦይ ለቦይ

ምነው በህልሜ መጣሽ ደህናም አይደለሽ ወይ”

“ አባይ ወንዙ ሞልቶ ግንድ ያገላብጣል

ጐረምሳው ተቀምጦ ሸማግሌው ያብዳል”

“አባይ ወዲያ ማዶ ዘመድ አለኝ ማለት ዋ! ብሎ መቅረት ነው ውሃ የሞላ ለት”... የሚሉና ሌሎች በርካታ ግጥሞችን ያንጐራጉር ነበር... የቅድመ አያቴ እንጉርጐሮው ሁል ጊዜ እልህና ቁጭትን ያዘለ እንደነበረ አስታውሳለሁ እኔም ታዲያ..“ትልቁ አያቴ ለምድነው ስትዘፍን የምትቆጨው ደግሞስ ሁል ጊዜ ስለ አባይ ወንዝ ብቻ ትዘፍናለህ? እያልኩ ስጠይቀው አይ...ይ... ልጄ ተስፋ አለም አሁን ብነግርህ... አይምሮህ ሊሸከመው አይችም ወደ ፊት ስታድግና ነፍስ ስታውቅ ሁኔታዎች ያሳውቁሀል...”ይለኝ ነበር፡፡

አንድ እለት እንደ ልማዱ ሲያንጐራጉር ‹‹ትልቁ አባባ ... እናት ወልዳ ወልዳ ልጇ ለሰው የሚያገለግልበት ለምንድ ነው?›› ስል ጠየቅኩት፡፡ እርሱም በረጅሙ ተንፍሶ ‹‹አዬ አዬ ልጄ ድሃ ስለሆነች ነዋ›› አለኝና እንጉርጉረውን ቆም አድርጐ ረዥም ሪዙን እያሻሸ ‹‹ልጄ ተስፋ አለም አንድ ጉዳይ ላጫውትህ ...

አባይ ወንዝ የኢትዮጵያ ልጅ ነው የተፈጠረውም የኢትዮጵያን ምድር ሊያጠጣ ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን እያገለገለ ያለው ለሌሎች ሀገራት ነው፡ ፡ ለዚህ ነው እናት ወልዳ ወልዳ ለሰው አገልጋይ እያልኩ የምቆጨው›› ሲለኝ ‹‹ለምን? ለሰው ሀገር ያገለግላል ጨካኝ ወንዝ ነው አባባ በውነት ያናድዳል›› ስለው፣ ‹‹አዬ ልጄ እርሱ አይደለም ጨካኝ እኛ ነን መጨከን ያቃተን›› ሲለኝ ‹‹እንዴት?›› አልኩት፡፡ ‹‹ይህን እንኳን ‘ለሁሉም ጊዜ አለው’ እንዳለ ጠቢቡ ሰለሞን ጊዜ ይመልስልሃል›› አለኝና ዝም አለ፡፡

አስታውሳለሁ... ቅድመ አያቴ መላከ ጥበብ በሞት አፋፍ ላይ ሆኖ ሲያጣጥር ” “ውሃ.. ውሃ...ውሃ...አ...ስጡኝ» ሲል አያቴ ከአባይ ወንዝ የተቀዳውን ውሃ ከእንስራው ውስጥ ጠልቃ በሽክናው ወደ አፉ ስታስጠጋለት ጭልጥ አድርጐ ከጠጣ በኂላ አይን አይኔን እየተመለከተ ለመናገር ከንፈሮቹን ሲያንቀሳቅስ በዚያው ነፍስ ከስጋው ተለየች፡፡ ዛሬ ላይ ሆኘ ሳስበው በዚያች ቅፅበት ምን ሊነግረኝ አስቦ ይሆን እላለሁ፡፡

መላከጥበብ በሞት ከተለየ በኂላ የቤታችን በእድሜ የአንጋፋነቱን ቦታ የተረከበችው ሴት አያቴ ናት ይቺው አያቴ እማማ ይርገዱ የወቅቱ ስራዋ የአባቷን ቦታ ተክታ ለልጆች ተረት ማውራትና ስለ አባቷ መላከጥበብ የህይወት ታሪክ መተረክ ነው፡፡

እርሷ እንደነገረችኝ ከሆነ ቅድመ አያቴ መላከጥበብ በአፄው ዘመነ መንግስት ወቅት ከሹማምንቶች መካከል አንዱ እንደነበር ነው፡፡ እናም ታሪኩ ሲቀጥል የአፄው መንግስት አማካሪና ባለሟል የነበረው ቅድመ አያቴ በወቅቱ “የአባይን ልጅ ውሃ ጠማት” በሚል ርዕስ መፅሐፍ ፅፎ ለማሳተም የአፄውን ይሁንታ ለመጠየቅና ለማስገምገም የፅሁፍን ይዘት ለሹማምቶቹ ያብራራል... ከአያቴ ትረካ እንደተገነዘብኩት የመፅሐፉ ይዘት የሚያጠነጥነው ግዮን ተብሎ ስሙ በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ የተጠቀሰው ወንዝ የተፈጠረበት ዋና አላማው የኢትዮጵያን ምድር ሊያጠጣ ስለሆነ ይኸ ወንዝ እያለ ሀገራችን መራብና መጠማት የለባትም ዓባይ ወንዝ ወደ ሰሜኑና ወደ ደቡብ ወደ ምስራቅና ምዕራብ አቅጣጫ እየፈሰሰ ምድሪቷን ሊያለመልም ይገባል ለዚህም ደግሞ መንግስታችን ህዝቡን አስተባብሮ መስራትና ማሰራት አለበት አባይ ሊገደብ ይገባል... በቃህ መባል አለበት... እስከመቼ አፈራችንንና ግንዳችንን ይዞ ይሄዳል... ይህን ለማድረግም ከፈጣሪ እርዳታ ጋር እንችላለን የሚል ሀሳብ ነበረው-የቅድመ አያቴ ፁህፍ፡፡

ይሁን እንጂ አፄውና የአፄው ባለሟሎች፣ ‹‹መላከጥበብ አብደሃል! የፈጣሪን ስራ ተጋፍተሃል አባይን ሊያስቆም የሚችል ሀይል ከሰማይ በታች የለም፡፡ በሹማምንቱ መሃል እንዲህ ያለ ቧልት ነገር ይዘህ በመቅረብህ አፄውንና መንግስታቸውን መዳፈር ነውና ያለ ይቅርታ ከስልጣንህ ወርደሀል... ወደ ፈለክበት ቦታ ሄደህ መኖር ትችላለህ... ነገር ግን እንዲህ ያለውን ሃሳብ አንስተህ ሕዝባችንን ማስተማርና ማነሳሳት እዳትችል አውግዘንሃል» ተብሎ ተቀባይነት በማጣቱ ቤተሰቡን ይዞ አባይ ወንዝ አፋፍ ላይ ቤት ሰርቶ መኖር ጀመረ፡፡ የአባይ ወንዝ ቁጭቱ አለቅህ ስላለው የነበረውን ሃሳብ ለመጭው ትውልድ ለማስተላለፍ በማሰብ “የአባይን ልጅ ውሃ ጠማት” የሚለውን “የላጭን ልጅ ቅማል በላው” በሚል ርዕስ በመቀየር የውስጥ ይዘቱን ሳይቀይር በብራና ላይ እየፃፈ ያሰራጭ ነበር፡፡ እንዲያውም ዛሬ ላይ ስለ አባይ የሚነገሩት ግጥሞች ከአመታት ቆይታ የተነሳ ወደ ህዝብ ሃብትነት ቢቀየሩም በወቅቱ ቅድመ አያቴ በመፅሐፉ ውጥ ያሰፈራቸው እንደነበሩ አያቴ በቁጭት ትተርካለች፡፡

ምስጋና ለፈጣሪ ይሁንና ቅድመ አያቴ ስለ አባይ ወንዝ በቁጭት እያንጐራጐረ ህይወቱ ብታልፍም በጊዜው በትውልድ ልብ ውስጥ ዘርቶት የነበረው ሃሳብ ወቅቱ ደርሶ ይኸውና መብቀል ጀምሯል፡ ፡ “ኢትዮያ ታላቁን የህዳሴ ግድብ በአባይ ወንዝ ላይ ለመገንባት የመሰረት ድንጋይ ጣለች” የሚለውን ዜና አያቴ በሰማችበት ዕለት ከደስታዋ የተነሳ ልቧ ቀጥ አለ፡፡ እኛም ድንገት በእጃችን ላይ አመለጠችን ብለን ስንደናገጥ እንደምንም ብለን ውሃ እረጭተን ነጠላ አርገብግበን ከሄደችበት ሸልብታ ስትመለስ፣

‹‹ የሰማሁት ነገር እውነት ነው ልጆቼ?›› ስትለን እኛም ‹አዎ እናታችን› አልናት፡ እልልታዋን አቀለጠችው፡ ፡ እኛም ድንጋጤአችን ሲለቀን አብረን እንደሰት ጀመር፡፡ አያቴ ሁለት እጇቿን ወደ ሰማይ ዘርግታ፣ ‹‹የአባቴ አምላክ እድሜ የሰጠኸኝ ይህን ልታሰማኝ ኖሯል ለካ!›› ብላ ካመሰገነች በኂላ ‹‹ጨረቃው መንግስታችን እግዜር ይባርከው፡፡ እድሜውን ያርዝመው ሺ አመት ይንገስ!›› እያለች የምርቃን ዶፍ ስታወርደው ያው መንግስት ማለት ህዝብ ማለት ነው ብዬ መንግስትን ወክዬ ‹‹አሜን›› እያልኩ ምርቃቱን የተቀበልኩት እኔ ነኝ፡፡

ወደ ገጽ 16 ዞሯል

አንድ እለት እንደ ልማዱ ሲያንጐራጉር ‹‹ትልቁ አባባ ... እናት ወልዳ ወልዳ ልጇ ለሰው የሚያገለግልበት ለምንድ ነው?›› ስል ጠየቅኩት፡፡ እርሱም በረጅሙ ተንፍሶ ‹‹አዬ አዬ ልጄ ድሃ ስለሆነች ነዋ››

# From Fault-Finding to Empowering: How Can We Build a More Learning-Centered Culture of Student Research at Bahir Dar University?

By Vachel Miller, Haftu Hindeya , and Ahmed Yibrie

Bahir Dar University faces a paradox. On the one hand, it holds a vision of becoming one of the top ten research university in Africa. Becoming a top research university requires that staff create an environment in which students feel well-equipped and motivated to conduct high quality research. But instead, we find ourselves acting as fault-finders and interrogators for students who are ill-equipped and fearful about research.

How can we face this paradox and find a new way forward?

In this essay, we intend to open dialogue in our academic community about changing the way we support post-graduate student research. Based on our international experience in post-graduate education, we suggest alternative pathways for enriching the strength and vitality of our research community.

**The problem with fault-finding**

In Ethiopia, there seems to be a negative tone to public conversations about research. At conferences, Friday Forums, and thesis defenses, examiners and audience members specialize in "fault finding". They look for any error, large or small, to highlight the deficiencies in a research project. Based on our experience, we've observed that many examiners engage in methodological interrogation, challenging the student: how did you choose your sample? Is your data contaminated? Why did you use this method instead of that one? And many more such questions!

Of course, critical questions about the quality of a research document are vital—but they need to come much earlier in the process, in an ongoing dialogue that strengthens methodological rigor long before the defense ever happens.

It's too late to challenge a student's research design at the end of the research process. At the time of defense, students can no longer change their methodological choices or data collection procedures. And if there are serious methodological problems, the defense becomes a deeply humiliating, even traumatic experience for students. Such an experience can be especially damaging to women, given the deficit of professional respect they may already experience in the academic and cultural environment.

There's another side effect: the "fault-finding" mode of defense interrogation will likely encourage students to "play it safe". They will be inclined to make conservative choices regarding their research designs when innovative, unfamiliar, "out of the box" approaches are likely to be criticized, even rejected, by examiners. As a result, students tend to replicate (and, in some cases, even plagiarize) earlier research, rather than feeling empowered to explore new questions, methods, or analytic approaches. When this happens, the research culture becomes a closed system. In short, if innovation is perceived to be a risk, students will stand far back from the "cutting edge" of knowledge production.

> **Team teaching could enhance a spirit of openness in our academic environment and contribute to the efforts of building a research culture ...**

We've also observed that there is something missing in our questions. Beyond questions of methodology, where are the questions about the significance of the research, about its implications for theory, policy, practice, and the improvement of life in our communities? In short, when do we engage in a respectful, professional dialogue with our students about what they have learned, and what we can learn together from their research?

After all, isn't such professional dialogue a key purpose of doing research in the first place?

**Why do research?**

In our academic culture, research has become a matter of endurance and self-protection for students, rather than a space of learning and growth. Our concern is that the current procedures do not create a conducive environment for developing a community of scholars. Quite the opposite! If the outcome of the research process is merely fault-finding, with little appreciation or professional dialogue about the value of the work, why should students do the research? Will they feel any intrinsic motivation to do more research in the future or develop a spirit of inquiry in their professional endeavors?

How can the research process become more collaborative, more respectful, and ultimately, a more meaningful process of discovery? How can we better nurture practitioner-scholars who use and produce knowledge as an integral part of their professional practice?

*We believe a research university can cook scholars more effectively if we take them off the interrogation grill.*

Turning down the "heat" of thesis examinations does not mean lowering our quality standards. On the contrary, standards can remain high, but we need to strengthen our support for quality research, as well as rethink our assumptions about HOW and WHEN we evaluate the quality of student research.

The current practice is to "test" the quality of research when it's over, at a defense. The defense is structured in an adversarial mode: examiners vs. student, with an advisor as a kind of silent referee. We suggest that rather than placing all of our emphasis on summative evaluation at the defense stage, we should re-orient our efforts to create a supportive community of scholars during the research process.

**Advising for learning**

At a practical level, we believe there are several ways to make the advising process more learning-oriented. Based on our experience in post-graduate programs in Europe and the United States, we suggest several strategies to shift our work in this direction:

- **Facilitate team teaching** particularly at the postgraduate level**.** In European universities, senior academic staffs often practice team teaching. When different professors teach together, it gives students an opportunity to learn from multiple perspectives, identify new topics for future research, and develop relationships with potential advisors. In BDU, a team-taught course would mean that professors could attend each other's presentations, with one professor serving as the "owner" of the course for managing assignments and grades. Team teaching could enhance a spirit of openness in our academic environment and contribute

continued on page 12

# እንግዳችን

## “ሴቶች ያመኑበትን ሥራ በፆታ የሥራ ውስንነት ሳያምኑ በፈቀዱት ሥራ በፈለጉት የሥራ መስክ በመሰማራት ጥሩ ውጤት ማምጣት ይኖርባቸዋል::”

ወ/ሮ ተስፋ ጌታሁን

የዚህ ወር እንግዳችን ወ/ሮ ተስፋ ጌታሁን በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያዋና ብቸኛዋ ሴት ሹፌር ሲሆኑ የህይወትና የሥራ ተሞክሯቸውን ከናይል ጋዜጣ ዘጋቢ ትዕግስት ዳዊት ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡ ቃለ መጠይቁን እነሆ፡፡ መልካም ንባብ!

ናይል፡- ስም፣ የትውልድ ቦታና የልጅነት አስተዳደግዎን ቢገልፁልን?

ወ/ሮ ተስፋ፡- ስሜ ወ/ሮ ተስፋ ጌታሁን እባላለሁ፡፡ የተወለድኩበት ባሕር ዳር ዙሪያ ወረዳ ዘጌ ልዩ ስሙ ኡራ ኪዳነምህረት ገዳም የሚባል አካባቢ ሲሆን በጥሩ የቤተሰብ እንክብካቤ ነው ያደግኩት፡፡

ናይል፡- የትምህርት ቤት ህይወትዎን አጠር አድርገው ቢገልፁልን?

ወ/ሮ ተስፋ፡- እድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ ከ1ኛ - 6ኛ ክፍል በአፄ ሠርፀ ድንግል ትምህርት ቤት፣ ከ7ኛ- 8ኛ ክፍል በፋሲሎ መለስተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የተከታተልኩ ሲሆን ከ9ኛ-12ኛ ጊወን ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተምሬያለሁ፡፡

ናይል፡- ስለ ትዳር ህይወትዎ እና ቤተሰበዎ ያጫውቱን?

ወ/ሮ ተስፋ፡- ባለትዳርና የሶስት ልጆች እናት ስሆን እግዚአብሄር ይመስገን ሰው አክባሪ፣ እናትና አባታቸውን የሚያከብሩና የሚረዱ ልጆች አሉኝ፡፡ በዚህም ከልጆቼ እና ቤተሰቦቼ ጋር ባለኝ የመተሳሰብ ህይወት እግዚአብሄር ይመስገን እጅግ በጣም ደስተኛ ነኝ፡፡

ናይል፡- ወደ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ መቼ ተቀላቀሉ? በምን በምን የሥራ ክፍሎች ሰርተዋል? አሁን በምን የሥራ ክፊል ላይ ነው የሚሰሩት?

ወ/ሮ ተስፋ፡- ወደ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተቀላቀልኩት በወቅቱ መምህራን ኮሌጅ በነበረበት ጊዜ በ1970 ሐምሌ ወር የምግብ ቤት አስተናጋጅ ሆኘ ነው የተቀጠርኩት፡፡ ከዚያም በኮሌጁ በመጣ የልዩ ክህሎት ስልጠና እድል ሹፍርናን ለመሰልጠን በመፈለጌ ይሄን ጉዳይ ለወንድሜ አቶ ንጋት ጌታሁን ይባላል ሳማክረው በፍፁም ይሄን እድል ማጣት እንደሌለብኝ ነገረኝ፡፡ በዚህ ላይ እኔም ይሄን ስልጠና ለመሰልጠን ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖረኝም ሥልጠናው ደብረማርቆስ በመሆኑ የ6 ወር ልጄን እንዴት ጥዬ እንደምሄድ ስጨነቅ ነፍሷን ይማረውና ወ/ሮ ውዴ ጌታሁን ትባላለች እህቴ የልጄን ሙሉ ኃላፊነት እንደምትወጣና ማሰብ እንደሌለብኝ አሳመነችኝና ወደ ደብረማርቆስ በመሄድ ሙሉ ስልጠናዬን ጨርሼ በመመለስ በ1980 ወደ ትራንስፖርት ክፍል በሹፍርና ተመድቤ ለ13 ዓመት ያክል እንዳሽከረከርኩ በሥራ እድገት በ1994 ዓ.ም ወደ ፖሊ ቴክኒክ ኢንስቲትዩት በትራንስፖርት አስተባባሪነት እስከ 2003 ዓ.ም ለ9 ዓመት ሰርቼ አዲስ በተሰራው መዋቅር የመኪና መለዋወጫ እስቶር ክፍል ተመድቤ አሁንም በዚሁ ክፍል በመስራት ላይ እገኛለሁ፡፡

ናይል፡- በዩኒቨርሲቲው የመጀመሪያዋና ብቸኛዋ የሴት ሹፌር ነበሩ የቤተሰብ ኃላፊነት ጋር ሹፌርነትን እንዴት ይገልፁታል? የቤተሰብ እና የማኅበረሰቡ ተቀባይነትስ?

ወ/ሮ ተስፋ፡- እግዚአብሄር ይመስገን ብዙም አልከበደኝም፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ የሴት ሹፌር ባለመኖሩ ማህበረሰቡም ሆነ ቤተሰቦቼና የዩኒቨርሲቲው ባለሥልጣናት በወቅቱ ይሰጡኝ የነበረው ሞራል በጣም ደስ የሚል እና የሚያበረታታ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የጐላ ይህ ነው የሚባል ችግር አልገጠመኝም እግዚአብሄር



ይመስገን የማይረሳና ደስ የሚል ጊዜ ነበር፡፡

ናይል፡- ሹፌርነት ብዙ ጊዜ የወንዶች ሥራ ነው የሚባለው፡፡ ሥራን የወንድና የሴት ብሎ መከፋፈል ከልምድዎ አንፃር እንዴት ይገልፁታል?

ወ/ሮ ተስፋ፡- ትክክል ነው አንድን ሥራ ለአንድ ፆታ ብቻ የመመደብ ልምድ በተለይ ባለፉት ጊዜያት በስፋት ይታይ ነበር፡፡ ለዚህም ይመስለኛል በወቅቱ እኔን ልዩ ያደረገኝ፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት ጊዜው ተለውጧል ማንኛውም ሰው ሴትም ሆነ ወንድ አንድን ሙያም ሆነ ሌላ ተግባር የወንድ ወይም የሴት ብሎ ሳይለይ (ሳይከፋፈል) ሁሉም ፆታ በፍላጐት የፈለገውን ሥራ እስካመነበት ድረስ መሥራት አለበት ብዬ አምናለሁ፡፡ ስለዚህም ሹፍርናም ለሴቶች ቀላል ነው፡፡ይሄንንም በአሁኑ ሰዓት በስፋት እያየን ነው፡፡

ናይል፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ 2017 አፍሪካ ከሚገኙ 10 ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ ለመሆን ራዕይ አስቀምጧል፡፡ ራዕዩን ለማሳካት በተሰማሩበት የሥራ መስክ ምን መሥራት አለብኝ ብለው ያስባሉ?

ወ/ሮ ተስፋ፡- አዎ እኔም እንደማንኛውም የዩኒቨርሲቲው ሠራተኛ ይሄ ራዕይ ተግባራዊ እንዲሆን ከፍተኛ የሆነ ፍላጐት ነው ያለኝ፡፡ ይህንንም ለማሳካት ከክፍል ባልደረቦቼ ጋር በመቀናጀት በተመደብኩበት የሥራ ክፍል በቅንነት በማገልገል ላይ እገኛለሁ፡፡

ናይል፡- ካለዎት የሥራ ልምድ ዩኒቨርሲቲውን እንዴት ይገልፁታል?

ወ/ሮ ተስፋ፡- ዩኒቨርሲቲው ከመምህራን ኮሌጅ ጀምሮ በልጅነቴ ተቀጥሬ ልጆቼን አሳድጌ ያስተማርኩበት ቤት ነው በዚህ ሂደት በወቅቱ እንደአሁኑ ፎቅ አልነበረም የተማሪው ብዛት

⇨

# እንግዳችን ...

እንደአሁኑ አልነበረም አሁን ግን ዩኒቨርሲቲው ከኮሌጅ ወደ ዩኒቨርሲቲ አድጎ በጣም ብዙ ተማሪ፣ ሠራተኛ፣ መምህራን እንዲሁም ህንፃዎችን በመሥራት በፍጥነት የሚያምርና ውብ የሆነ ዩኒቨርሲቲ እና የምርምር ተቋም ለመሆን በቅቷል፡፡ ይሄንን ለውጥ እድለኛ ሁኘ ኑሬ በማየቴ እግዚአብሄር ይመስገን ደስተኛ ነኝ፡፡

ናይል፡- በሥራ ዓለም ሲኖሩ አሳዛኝም ሆነ አስደሳች ገጠመኝ ካለዎት ቢያካፍሉን?

ወ/ሮ ተስፋ፡- በዚህ ሙያ ላይ እያለሁ ከገጠሙኝ ገጠመኞች የማልረሳው ወደ ኮሶ በር ለስብሰባ አለቆችን ይዤ በምሄድበት ጊዜ እዚያው ከተማው ላይ የነበሩ ሰዎች የተሳፈሩ ባለስልጣናትን እናንተ ወራዶች እንዴት በሴት ሹፌር ትሄዳላችሁ ብለው መኪናውን ተጠግተው ሲናገሯቸው እነሱም በሁኔታው በመሳቅ ከቦታው ሂደናል፡፡

ናይል፡- ለሌሎች ሴቶች በፈለጉት የሥራ መስክ ላይ መሥራት ይችሉ ዘንድ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

ወ/ሮ ተስፋ፡- ሴቶች ያመኑበትን ሥራ በፆታ የሥራ ውስንነት ሳያምኑ በፈቀዱት ሥራ በፈለጉት የሥራ መስክ በመሰማራት ጥሩ ውጤት ማምጣት እንዳለባቸው ብቻ ራሳቸውን በማሳመን ተስፋ በፍፁም ሳይቆርጡ እንዲሰሩና ውጤታማ እንዲሆኑ መልካም ምኞቴ ነው፡፡

ናይል፡- ይህ ቀረ የሚሉትና ማመስገን የሚፈልጉት ካለ ዕድሉን ልስጥዎ?

ወ/ሮ ተስፋ፡- ይህ ቀረ የምለው የለኝም ማመስገን የምፈልገው በቅድሚያ እግዚአብሄርን ቀጥዬ እመቤታችን ሙሉ ቤተሰቦቼን እና በሹፍርና ሙያ ላይ እያለሁ ሞራል ሲሰጡኝ የነበሩ ሰዎችን በሙሉ ጓደኞቼን በተጨማሪም አስታውሳችሁ ለዚህ ስለጋበዛችሁኝ እናንተንም አመሰግናለሁ፡፡

ናይል፡- እኛም እናመሰግናለን፡፡

# የግጥም ጥግ

## የልቤ ጓደኛ

ይኸነዉ ወዳጅስ የልብ ጓደኝነት፣
ስኖር አብሮኝ ያለ ከሞትሁም የሚሞት፤
ለእኔም አንተ አለኸኝ፣
ሳገኝ የወደድኸኝ፣
ሳጣ የጠላኸኝ፣
ስታመም የራቅኸኝ፣
ሳልሞት የቀበርኸኝ፤
ደስታዬ ሀዘንህ፣
ሀዘኔ ጭፈራህ፣
የልቤ ጓደኛ በእዉነት አንተ ነህ፡፡
ከጣልከኝ ትቢያ ላይ ዘልዬ ስነሳ፣
ድመት የነበርሁት ሆንኩልህ አንበሳ፣
ለአንተ ወይስ ለአምላክ ለማን ልክፈል ካሳ፡፡

ይኸነዉ ገ/ሥላሴ (ዶ/ር)

ከግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ

# የጉዞ ማስታወሻ

በሙሉጎጃም አንዱአለም

ሐምሌ 15 ቀን 2008 ዓ.ም ከማለዳው 12፡00 ሰዓት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ እምብርት ከሆነው ጥበብ ህንፃ ቅጥር ግቢ ውስጥ ደረጃ አንድ ተመሳሳይና ማራኪ ቀለም ያላቸው ሰባቱም የጉዞ አውቶቢሶች የተሰጣቸውን ቁጥር ከፊትና ከኋላ በመለጠፍ እንዲሁም የኢትዮጵያንና የዩንቨርሲቲውን ባንዲራ በወገባቸው ላይ ሸብ አድርገው ቅደም ተከተላቸውን በመጠበቅ ሁሉም ተጓዥ በተመደበበት መኪና መግባቱን ካረጋገጡ በኋላ ከጥበበ ህንፃ ተነስተው ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ጉዞአቸውን ጀመሩ፡፡ ወቅቱ የክረምት ወራት በመሆኑ ዳንግላ ከተማ ደርሰን ለቁርስ 30 ደቂቃ ብቻ መቆየት እንዳለብን ከጉዞው አስተባባሪ ኮሚቴዎች ትዕዛዝ ቢሰጥም የአየሩ ንብረት ቀዝቃዛ በመሆኑ ይመስላል አብዛኛው ተጓዥ የምግብ ፍላጎቱ ብዙም አልነበረም፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ከተፈቀደው ሰዓት አልፈው በመሯሯጥ ላይ የነበሩም አልታጡም፡፡

የአዲስ አበባን መንገድ የቀድሞዋ እንጅባራ የአሁኗ ኮሶበር ከተማን ወደ ጐን በመተው ጉዞአችንን ወደ ግልገል በለስ ስናቀና መንገዱ ገና በመሰራት ላይ ስለነበር ምቹ ባይሆንም ያለውን ችግር በመቋቋም ስንጓዝ እንዳጋጣሚ ሆኖ በአንድ አካባቢ የተቀመጥነው ሁሉ ለአገሩ እንግዳ በመሆናችን የምናልፋቸውን ከተሞች «ይህ ማን ይባላል?» ብለን የርዕስ በርዕስ ጥያቄ ብናቀርብም መልስ የሚሰጥ ባለመኖሩ እነ ቻግኒንና የመሳሰሉትን ከባንኮችና ከሌሎች ከተማውን ከሚገልፁ የሪክላም ፅሁፎች ላይ እያነበብን መረዳት ችለን ለስብሰባ የተጠሩ የመሰሉ፣ ሰንሰለታማ ተያያዥነት ያላቸውንና በአረንጓዴ ህብረ ቀለም አሸብርቀው የሚማርኩትን ተራራዎች በተመስጦ እየቃኘን ግልገል በለስ ከተማ ከግማሽ ቀን በኋላ ደረስን፡፡

ሁሉም ሰው የከተማውን መጥበብና መስፋት በውል ስላልተረዳ ማረፊያ አልጋ ፍለጋ በቡድን በቡድን በመሆን በአራቱም አቅጣጫ ተሰራጨ፤ ወዴት መሄድ እንዳለበት ግራ የተጋባና ከመሀል መንገድ ቆሞ ጥቂት ሰዓት ያሳለፈም ይስተዋል ነበር፡፡

ሁሉም እግሩ በመራው እየሄደ አልጋ ከተከራዬ በኋላ ከነጋ ምንም ዓይነት ምግብ ያልቀመሰውም፤ ዳንግላ ላይ የተቋደሰውም በተመሳሳይ መልኩ ምግብ ይገኛል ተብሎ በሚገመትበት ቦታ ሁሉ ተሰራጭተን ዋናው የሚበላ ምግብ መሆኑ እንጅ ምርጫ ሳናበዛ ያገኘነውን ሁሉ ከተመገብን በኋላ ወደ ተከራየነው ማረፊያ ክፍል በመሄድ እረፍት አደረግን፤ አገሩን ለማየት መንቀሳቀስ እንኳ ብንፈልግ ነገ ወደ ግድቡ ለመጓዝ ከሌሊቱ 8፡00 ላይ ሁሉም ተጓዥ በተመደበበት መኪና ውስጥ እንዲገኝ የሚል ትዕዛዝ ከኮሚቴዎች ስለተሰጠ ያንን በማሰብና ድካሙም በመጨመሩ ወጥተን እራት እንኳ ሳንበላ ለክፉ ጊዜ ቢሆን ብለን ከያዝነው ቆሎ በልተን ተኛንና በተገለፀው ሰዓት ለመድረስ ከሌሊቱ 8፡00 ላይ በአንድ ግቢ በርካታ ተጓዦች አልጋ ይዘን ስለነበር ርዕስ በርዕስ ተቀሳቅሰን በሰዓቱ ብንደርስም ይህን የሌሊት ጉዞ እረስተው ከተማ ሲዝናኑ ያመሹት በሰዓቱ ባለመድረሳቸው እነሱን በመጠበቅ ጊዜ ወሰድን 9፡10 ላይ ጉዞ 2 ወደ ህዳሴው ግድብ ተጀመረ፡፡ መንገዱ ምን እንደሚመስል እንኳ ለማየት ጨለማ በመሆኑ ብቻ ፅንስ የያዘች ሴት ካለች ፅንሱን ይዛው እንደማትመለስ እርግጠኛ ሆኖ መናገር እስከሚቻልበት ደረጃ ድረስ መንገጫገጭ ስለነበር ከኋላ ወንበር ያለ ሚዛኑን ጠብቆ መቀመጥ ስለማይታሰብ ካልቆመ ተፈንጥሮ ወደፊት ስለሚሄድ የውዴታ ግዴታ ዝላይ እየዘለልን መቋጫ የሌለውን ጉዞ ተያያዝነው፡፡ በግምት ግማሽ መንገድ ላይ ስንደርስ አብራኝ ያለችው ጓደኛዬ ከመንገዱ መክፋት ጋር እርዝማኔው ተደምሮ እምባዬን አስመጣው አለችኝ፡፡ እኔም ሆድ ቢብሰኝም እንደምንም ተቋቁሜ ጓደኛዬን ለማፅናናት «ማንም ሳያስገድድሽ የሀገር ፍቅር ይዞሽ ነው የመጣሽው!! ስለዚህ እንዴት ታለቅሻለሽ?» ብዬ በጥያቄ መልኩ ለማፅናናት ሞክሬ ትንሽ ፈገግ እንድትል አደረግኳት፡፡መድረስ አይቀርም ከህዳሴው ግድብ 30 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ከሚገኘው የመጀመሪያው ፍተሻ ከሚካሄድበት ኬላ ላይ 3፡25 ላይ ደረስን፡ የተጓዡ ቁጥር በርካታ በመሆኑ ፍተሻው እስከሚጠናቀቅ ድረስ ረጅም ሰዓት ወሰደብንና ጊዜው ሩጫውን ቀጠለ፡፡ እኛም ከመጀመሪያው ኬላ ስለደረስን ተሚጠ የነበረው የመድረስ ተስፋችን ለምልሞ ከተወሰነ ጉዞ በኋላ አንዳንድ ተራራ ላይ የተሰሩ የግድቡ ሥራዎችና የዓባይ ወንዝ ከርቀት ስለታየን የአካባቢውን መልክአምድር በአርምሞ እየተመለከትን ስንጓዝ ከሁለተኛው ኬላ ላይ ደረስን፡፡ ሁሉም መኪና መምጣቱ ከተረጋገጠ በኋላ በአንድ ላይ ጉዞአችንን እንደምንጀምር ከኮሚቴዎች ተነገረንና እረፍት ለማድረግ ብንሞክርም ፍተሻ የሚካሄደው ሁሉም ሰው ከመኪናው ወርዶ ስለሆነ እና ፀሐይዋ ክረምት መግባቱን የተገነዘበች ስለማትመስል በትናንሽ ቁጥቋጦዎች ስር ሽጉጥ ሽጉጥ ብለን የመጨረሻውን መኪና ስንጠባበቅ እኔ ከባህር ዳር እስከ ግልገል በለስ የመጣሁበትን አራት ቁጥር መኪና ጓደኞቼ 3 ቁጥር ስለነበሩ በዚያ ገብቼ በሰላም ቀድመን ደርሰን ነበር፤ ነገር ግን 4 ቁጥር መኪና መንገድ ላይ ብልሽት ደርሶበት ተጓዦች በሌላ መኪና ተከፋፍለው እንደገቡና የመዘግየቱ አንዱ መንስኤ እንደሆነ ሰማሁ፤ «ዋናው ሰላም መሆናቸው ነው» በሚለው ሀሳብ ሁሉም ተስማምቶ ለመድረስ ስንጓጓለት ወደነበረው የህዳሴ ግድብ 6፡15 ላይ ደረስን፡፡

መኪናዎች የሚሄዱበትን አቅጣጫ የሚመራ አካል ከሁለተኛው ኬላ ላይ ትንሽ መኪና በመያዝ ከፊት ለፊት እያመራ ከታለመው ቦታ ደረስን ለእንግዳ መቀበያ ከተዘጋጀው ቦታ ገብተን የግድቡ ዋና ሥራ አስኪያጅ እንጅነር ስመኘው በቀለ ግድቡን ለመሥራት ከተጠነሰሰበት መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለበትን ሁኔታ በዝርዝር አስረድተው ፕሮጀክቱ ከግድቡ ሥራ ጐን ለጐን አካባቢውን በደማቅ ከተማ ለመከተም የሚያስችሉ እንደ አውሮፕላን ማረፊያና ሌሎች አንድ ትልቅ ከተማ ማሟላት የሚገባውን ነገሮች በመሥራት ላይ እንደሆኑ ከገለፃቸው መረዳት ችለናል፡፡

ወደ ገጽ 13 ዞሯል

# ፍናፍንት

## ምእራፍ አንድ

በታምሩ ከፈለኝ (የሻረግ)
(www.facebook.com/ደቀ ከፈለኝ ወየሻረግ)
የ3ኛ አመት የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል ተማሪ

"ድም" የሚል የመሳሪያ ጩኸት ያካባቢውን ፀጥታ አናጋው፡፡ እንዳይላሉ ቤት ታድመው የባለወልድን ዝክር የሚቃመሱ እድምተኞች ጨዋታቸውን ገትተው ጆሯቸውን ወደ ውጪ ቀስረው ማድመጥ ጀመሩ፡፡ የእንዳይላሉ ሚስት የሹሜ የእንግዶቿን ፅዋ ልትሞላ የያዘችውን የጠላ ማንቆርቆሪያ ቁጭ በማድረግ ወገቧን ያዝ አድርጋ፤ ጆሮዋን ወደ ውጪ ቀስራ ቆመች፡፡ እንዳይላሉም እንደሚስቱ ሁሉ ማህበርተኛውን ለማስተናገድ ሽር ጉድ በሚልበት አጋጣሚ የመሳሪያ ድምፅ በመስማቱ በመለኮት ተረግሞ የቆመ የሰው ሃውልት ይመስል ቤቱ መሃል ላይ ደርቆ ቀረ፡፡

የመሳሪያውን ድምፅ ተከትሎ አንዲት ሴት ኡኡታውን በረጅሙ ትሰነጥረው ጀመር፡፡ ከባለወልድ እድምተኞች መሃል መሰረት

"ዘራፍ!

ትንታጉ መንዜ የሳቱ ላንቃ፣

የተናገረው አንዱ እሚበቃ፡፡

አባትም የለው እናቱን አያውቅ፣

እግዜርን አምኖ ይኖራል በሃቅ፡፡

የመቶ ሰው ዋስ ያምሳ ሰው ግምት፣

ከወንዶቹ ወንድ ከሴቶቹ ሴት፡፡"

ብሎ ፎክሮ ታጣፊ ክላሹን አቀባብሎ፤ ከፊቱ ያለውን አግዳሚ ወንበር ተራምዶ፣ ደረቱን ገልብጦ ወጣ፡፡ ሌሎች እሱን ተከትለው ሲወጡ አቶ እንዳይላሉ እዛው እቆመበት ሳይናገር ሳይጋገር ቆሞ ቀረ፡፡

መሰረት ካስር አመት በፊት ወደዚህ አካባቢ ሲመጣ መንዜ ነኝ ይበል እንጂ አንድም ቀን እዚህ አካባቢ ዘመድ አለኝ ሲል ተሰምቶ አይታወቅም፡፡ ብዙዎች በፉከራው ግራ ቢጋቡም ደፍረው "ለምንድነው እንዲህ ብለህ የምትፎክረው?" ብለው የጠየቁት ግን ጥቂት ናቸው፡፡ እሱ ግን የሁሉንም ጥያቄ ከመመለስ ይልቅ ዝምታን ነበር የመረጠው፡፡

ሲላመዳቸውና ከማህበረሰቡ ጋር ሲግባባ ሰው ጥግ የማይደርስ ከነኩት የማይለቅ አካባቢውን የማያስደፍር ጀግና መሆኑን ሲያውቁ ከወንዶቹ ወንድ ብሎ መፎከሩ እውነት መሆኑን አይንገሩት እንጂ ሁሉም በየልባቸው አደነቁለት፡፡

ብዙዎች የሚጠጡት የባለወልድንም ማህበር ተረኛ ሆኖ ሲደግስ "ቤቱ ሴት የለው ምኑን ከምን አርጎ ማህበሩን ያወጣው ይሆን?" እያሉ ሲጠብቁ አንድም ቀን ሰው እርዱኝ ብሎ ደቦ ሳይጠራ ጠላው ሳይቀጥን እንጀራው ሰይነኮር ወጡ ሳይጎረና ቆሎው ሳያር ደግሶ ማህበሩን አወጣ፡፡

የማህበሩ ዕለት ሰው እሱ ቤት ተሰብስቦ የቤቱንም ውበት እና ንፅህና እያደነቀ ሲበላና ሲጠጣ በጨዋታቸው ህፃን አዛውንቱ የሚወዳቸው ሽማግሌ "እኔ ምለው" ብለው ንግግር ሲጀምሩ ሁሉም ምን ሊሉነው ብሎ ፀጥ ብሎ ያደምጣቸው ጀመር፡፡ ሽማግሌው ሁሉም እያደመጧቸው እንደሆነ ሲያውቁ "እኛ እማናውቃት ሴት ቤት ቤቱን ኖራለች እንዴ?" አሉ፡፡ ሁሉም የልባቸውን ስለተናገሩላቸው በሳቅ አውካኩ፡፡

መሰረት በሽማግሌው ጨዋታ ፈገግ ብሎ ማህበርተኞቹን እያስተናገደ "እኔስ ግማሹን ሴት አይደለሁ፣ ካባት ብቻ አልተፈጠርኩ" ብሎ መለሰላቸው፡፡

አንዳንዶች ውስጥ ውስጡን "እኔ ነኝ የደገስኩት ለማለት ነው ይሄ ሁሉ" እያሉ ከንፈራቸውን አያሽራመው አለፉት፡፡

አንድ ወር አንዲት ማህበርተኛቸው ታማ አልጋ ላይ በመዋሏ ማህበሯን ደግሳ ማውጣት ስላልቻለች ያካባቢው ሴት ተረባርቦ ሊያወጣላት ሽር ጉድ ሲል እሱም እኔም እረዳለሁ ብሎ ስራውን ተያያዘው፡፡ ሴቶቹ ሁላ የጋገሩትን እንጀራ እያሳዩ "የኔ ያምራል!. . . የኔ ያምራል!" እየተባባሉ ሙያ ሲለካኩና ሲፎካከሩ እሱ ከጋገረው እንጀራ ጋር እንጀራዋን ለማወዳደር የደፈረች ሴት አልነበረችም፡፡ ጠላውን ሙሉ ሃላፊነት ተቀብሎ የዶሮ አይን የመሰለ ጠላ ጠምቆ ሙያውን አስመስክሯል፡፡ የወጡም ስራ ፊት አውራሪ እሱ ነበር፡፡ በዚህም "ከሴቶቹ ሴት" ብሎ መፎከሩ እብለት እንዳልሆነ ብዙዎች አረጋገጡለት፡፡

በቆይታው ከማህበረሰቡ ጋር ከመግባባቱ በተጨማሪ ወንጀልን በመከላከልና ወንጀለኞችንም አሳዶ እስከመያዝ በዋለው ውለታ መንግስት ለታጣፊ ክላሹ ፈቃድ ሰጥቶ አስታጥቆታል፡፡ ምንም ያህል ከሰዎቹ ጋር ቢግባባም ባለወልድን ከደገሰበት ቀን ውጪ ቤቱ ሰው አያስገባም፡፡ ላንዳንድ ጉዳይ ቤቱ የመጡትንም ዉጪ እናውራ እያለ ይመልሳቸዋል፡፡

የባለቤቷን መፍዘዝ ያየችው የሹሜ "ኤድያ አሁን እርሶ ወንድ ነዎት ወይስ ሴት? እስኪ ወጣ ይበሉ" ብላ ግድግዳው ላይ ተወልውሎ የተሰቀለውን አጭር ምንሽር አውርዳ አቀባበለችው፡፡ መሳሪያ ሲቀባበል የሰማው እንዳይላሉ በድንጋጤ ከቆመበት ዞር ሲል ሚስቱ መሳሪያውን አቀባብላ እንዲቀበላት ዘርግታለታች፡፡

"ምን ላርገው የሹም?" አላት፡፡

"አረ ወዲያ! ይያዙታ ለክፉውም ለደጉም ይጠቅማል ወንድ አይደሉ እንዴ? እኔንም ሰው አፍ አያግቡኝ"

"ወንድማ ወንድ ነኝ ግን. . ."

"ግን ምን?!" አይኗን አፍጥጣ ልትሰገስግበት ይመስል አንገቷን አስግጋ ቀረበችው፡፡ "ለምን እንደተተኮሰ ምን ይታወቃል ደሞ ከድምጡ ሰው ላይ ያረፈ ይመስላል እስኪ እንደወንዶቹ ይሁኑ ባክወት ይቀበሉኝ" አለች፡፡

"አረረረረረረ ባይሆን ዱላው ይሻላል. . . ከዘራዬን. . ." አለ፡፡

ከውጪ በድጋሚ "ክው" የሚል የመሳሪያ ድምፅ ተሰማ፡፡ የሹሜ ባሏን በቆመበት ትታው መሳሪያውን ይዛ ወጣች፡፡ ገና የቤቱን ደፍ ከመርገጧ ተከታታይ የተኩስ ድምፅ ተሰማ፡፡

"አረ ተመለሽ የሹም!" አላት፡፡

"ወዴት ነው የምመለሰው ሀገር በተኩስ ስትታወክ" ቀሚሷን ሰብስባ እየተንደረደረች ወጣች፡፡ አቶ እንዳይላሉ ከመርገጫው ጥምጥም የብረት ጆንፎ የጠገበ ከመጨበጫው በጅና የተዋበ ከዘራቸውን አውርደው ተከትሏት፡፡

የጥር ባለወልድ የሚነግስበት መስክ ላይ አዳፋ ሸማ የለበሱ ሰዎች ተሰብስበዋል፡፡ ሴቶች ጭንቅላታቸውን እየያዙ ኡኡታውን ያስነኩታል፡፡ ወንዶች ጥምጥማቸውን ቦድነው ጭስ ጠገብ ከዘራቸውን እያቆነደሹ በያሉበት ያነቡቃሉ፡፡ መሰረት የተሰበሰቡትን ሰዎች ገፋፍቶ የሚመለከቱትን ሲመለከት የቆመበት ጠፋው፡፡ የሹሜም መሰረት ያየውን ስትመለከት ልቧን ስውር አረጋት፡፡ እግራቸው ስር ተዘቅዝቆ ከወደቀው ወጣት ጭንቅላት ደም ጠለል ብሎ ወርዶ

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

# ነገ ባይኖር ኖሮ

በቤተልሄም ሃይለማርያም
፫ኛ አመት የኢኮኖሚክስ ተማሪ
www.Facebook.com/Bethelhem Hailemariam

ፈዘዝ ባለው የግርጌ መብራት ላይ አይኖቹን ወረቀት ላይ ተክሎ ከቃላት ጋር ይታገላል፡፡ ሁለተኛ መፅሃፉን እያገባደደ ስለሆነ በከፊልም ቢሆን የልጅነት ህልሙን መኖር እንደጀመረ ይሰማዋል፡፡ በመጀመሪያው መፅሃፉ ካንባቢያን ያገኘው ምላሽ እምብዛም ስላላረካው በዚህኛው እንደሚያካክስ ተስፋ አድርጓል፡፡ የህይወት ልምዶችን በተለየ መንገድ መተንተን የፍልስፍናውን አለም መቀላቀል ያስደስተዋል፡፡ እናም አሁን የሚታገለው ፅሁፍ የሰው ልጅን ህይወት ከተስፋ ጋር ያቆላለፈውን ሰንሰለት ውል ለማግኘት ይመስላል፡፡

"ሁሌም የማለዳዋ ጀምበር የምትናፍቀን ልንጓጓለት የሚገባ ነገር ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ፈጣሪ ታላቁ የመፍጠር ጥበቡ የሚገለፀው ጊዜ ከተባለ ገዢ ስር ሎሌነት ያደሩትን የሰው ልጆች ተስፋ የሚባል መዳኛ የሰጣቸው ጊዜ ነው፡፡ የተጎሳቆሉ እድሜዎች፣ የቆሰሉ ዛሬዎች፣ የተሰበሩ ትናንቶች የሚጠገኑት በነገ ነው፡፡ ትናንት አልፎ ዛሬ፣ ድሮ አልፎ አሁን ባይተካ ኖሮ፣ ዘመናት ተሸረው ዘመናት ባይነግሱ ኖሮ፣ እድሜ እንደ ሰጋር በቅሎ በትውልድ ባይከለል ኖሮ. . ."

ጢሙን እያሻሸ ጠጉሩን እየደባበሰ ከገባበት የሃሳብ ባህር የበለጠ ለመጥለቅ ይጥራል፡፡

". . . ኖሮ፤ በተስፋና በምኞት ፅንፎች በሃሊዮ መኖር ባንችል ኖሮ፤ ድሃ በህልሙ ቅቤ ባይበላ ኖሮ . . . ከነዚህ ሁሉ ቢሆን ኖሮ ምናልባትም እንፈጠር ነበር፡፡ የእነዚህ ሁሉ ጥንካሬ ደግሞ የተስፋ ሃያል ክንድ ነው፡፡ ተስፋ የማይንደው እያሪኮ የማይከፍለው ቀይ ባህር የለም፡፡ ምናልባትም ነጋችንን እናውቅ ዘንድ እድሉ ተሰጥቶን ቢሆን ኖሮ ልናየው የምንጓጓለት ነገር ስለማይኖረን መኖራችን ምክንያታዊ አይሆንም፡፡ የሰው ልጅ ደካማ ጎን በቃኝ አለማለትና አለመርካት እንደሆነ ብዙዎቻችን ብንስማማም ልብ ያላልነው ነገር ግን አለ፡፡ አሁን ሙሉ እንደሆንን ካሰብንና የበኋላ መምጣት በህይወታችን ምንም እንዲለወጥ ካልፈቀድንለት ነገ ለመገኘት የማይገባን ነንና ቀሪ ዘመናችንን ለመኖር አመክንዮ አይኖረንም፡፡"

መፅሃፉን ሲያጠናቅቅ ምን አይነት ጠንካራ መልእክት ሊኖረው እንደሚችል እያሰበ አልፎ አልፎ ፊቱን እያሻሻ መፃፉን ቀጠለ፡፡

". . .ከኦሪታዊው አብርሃም ተስፋይቱ ምድር እስካሁኖቹ የሃዲስ ኪዳን ልጆች የዘላለም ህይወት ተስፋ በሃይማኖታዊውም ሆነ በማህበራዊው የህይወት ጎዳና ፋኖሱን ይዞ ሰልፉን የሚመራው አለቃ ተስፋ ነው፡፡ ዛሬ ከተወለደች ጨቅላ ሞቷን እስከምትጠብቅ የ90 አመት አሮጊት ድረስ አእምሮ ውስጥ ለሰከንድ እንኳን የማይርቀው ባልንጀራ ተስፋ ነው፡፡ እያንዳንዳችን ጠዋት ከንቅልፋችን የሚያነቃን ነገ ብለነው የነበረውን ዛሬን የማየት ተስፋ ነው፡፡ በጉጉት የተሞላ አዲስ ቀን ፍሬዎቻችንን ሁሉ ትናንት ሲሆኑ አዲስቷ ጀንበር ነገን በተስፋ አገልግል አዝላ ብቅ ትላለች፡፡"

ሰአቱን አየ - 8:30፡፡

እንቅልፍ እየተጫጫነው ነው፡፡ ወረቀቶቹን ሰብስቦ ብዕሩን አሳረፈ፡፡ የጀመረውን ፅሁፍ ነገ እንደሚጨርሰው ተስፋ አድርጎ ጫማውን እንኳ ሳያወልቅ አልጋው ላይ ጋደም አለ፡፡ አእምሮው ግን በሃሳብ ይናውዝ ጀመር፡፡

ነገ. . . ነገ. . . ነገ. . . የማያልቅ ነገ. . .

# የማላታየን ቅኝት፡ ከባዮኬሚስትሪ የትምህርት ክፍለ ጊዜ እስከ የማሳ ላይ ድምጹ

በመክሊት ጋረደው
በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ
የሶስተኛ ዓመት የህክምና ተማሪ

አያቶቻችን እና ቅድመ አያቶቻችን ለሀገራችን የግብርና ዘርፍ ማደግና አመርቂ ውጤት መገኘት ሚናቸው እንዲህ ነው ብለን የማንለው የሰፋና ከፍተኛ ነው፡፡ የእነሱ በሰላምም ሆነ በጦርነት፣ በድርቅም ሆነ በጥጋብ ያልተበገረ ስራ አክባሪነት! ጥንካሬ እና ትጉህ ስራ ዛሬ ሀገራችን የደረሰችበት የግብርና ዘርፍ ስኬት ከበቂ በላይ መስካሪ ነው፡፡ እንደ አሁን ዘመናዊ የፀረ - አረም እና የፀረ - ተባይ ኬሚካሎች በማይገኙበት ጊዜያት ሀበሻዊ በሆኑ የባህላዊ አረምና ተባይ መከላከያ ዘዴዎች አጠቃቀማቸው በዘመኑ የማይታሙ የግብርና ዘርፉ ተዋንያን ሆነው አልፈዋል፡፡ ዛሬ ላይም ያለው የግብርና ዘርፍ ዕድገት እጅግ አመርቂ እና አዳዲስ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ስልቶች ወይም መንገዶች ተግባራዊ እየሆኑ የሚገኙበት ወቅት ሲሆን በፊት ከነበረው የግብርና አሰራር የተለየ እና የተሻለ የምርትና የጥራት ደረጃ የፈጠረ ጭምር ነው፡፡

የሀገራችንን የግብርና ዘርፍ ዕድገት ቀጣይነት ለማስጠበቅና ብሎም ለማሳደግ እየተደረገ ባለው ሂደት ውስጥ የዘመናዊ ፀረ-አረም እና ጸረ-ተ ባይ ኬሚካሎች አጠቃቀም ቁጥጥርና ግንዛቤ ለህብረተሰቡ ማስጨበጥ ትልቁን ስፍራ የሚይዝ ሲሆን እነዚህን ኬሚካሎች በተገቢው መጠን እና አጠቃቀም አለመጠቀም የሚፈጥራቸው የጤና እክሎች እነዚህንም ተከትለው የሚመጡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን ለመከላከል ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር መስራት ፋታ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም፡፡ በዚህ ጉዳይ በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው አካላት እየሰሩበት እና ከሌሎች አካላትም ጋር በመሆን ለመስራት ከምን ጊዜውም በላይ ዝግጁ የሆኑበት ወቅት ጭምር ነው፡፡

በ2007 ዓ.ም. የፕሪ ክሊኒካል አንደኛ ዓመት ተማሪ በነበርኩበት ወቅት የባዮኬሚስትሪ መምህር የሆኑት መምህር ዮሐንስ ስለ ማላታየን ሲያስተ ምሩን በምኖርበት አንባቢ የምትኖር አንዲት እናት በአርሶ አደሮች በኩል ስላለ የማላታየን አጠቃቀም ጉድለት ያወራችኝ ታውሶኝ ከትምህርቱ ክፍለ ጊዜ መልስ ተከትያቸው ሄጄ ስለሰማሁት ነገር ካስተማሩን የማላታየን ጉዳት አንጻር እይታቸው ምን እንደሆነ ጥያቄ ሳቀርብላቸው የሰሙት ገርሟቸው እንዲህ አይነት አጠቃቀም ናለ የአጠቃቀም ጉድለቱ ሊያስከትል ስለሚችለው ጉዳት እና አጠቃቀምን በተመለከተ የእውቀት ማነስ ቢኖር እንጂ አርሶ አደሩ እንዲህ ሊጠቀም እንደማይችል ጠቀሱልኝ፡፡

ከዚህ ዕለት በኋላ ለአርሶ አደሩ የማላታየን አጠቃቀምን በተመለከተ ግንዛቤ መፍጠርያ የሚሆን ስራ መስራት እንዳለብኝ የገጠመኝ ሁኔታ ስላስገነዘበኝ አርሶ አደሮችን መድረስ የሚቻልበት መንገድ መፈለግ ጀመርኩ፡፡ በመምህርት ጥሩወርቅ አበረታችነት ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የጎልማሶች ትምህርት ክፍል ጋር በመተባበር ኤፍ ኤም ሬድዮ ላይ የተሰጠኝን የአየር ጊዜ ዕድል በመጠቀም በጉዳዩ ላይ የተወሰነ ስራ በአንድነት ለመስራት ችለናል፡፡ በዚህ አጋጣሚ መምህርት ጥሩወርቅን አመሰግናለሁ፡፡ በኤፍ ኤም ራዲዮ ላይ የአየር ጊዜ በመጠቀም ስለሁኔታው ግንዛቤ ለመፍጠር ሞክሬ ነበር፡፡

ግንዛቤ ለመፍጠር መረጃ ስሰበስብ በአማራ ክልል የግብርና ቢሮ ስር የባህር ዳር እፅ/ተ/ቅ/ጥ/ምርምር አስተባባሪ የሆኑት አቶ አየሁ ዘሪሁን ጋር ሰፋ ያለ ቆይታ አድርጌያለሁ፡፡ አቶ አየሁ የአጠቃቀም ጉድለት እንዳለ እና በየቀበሌው የልማት ጣቢያች ስርጭት ከቀድሞ በተሻለ መልኩ ለአርሶ አደሩ ቅርብ በመሆን እየሰሩ እንደሆነ ነግረውኛል፡፡ የአርሶ አደሩን የኬሚካል አጠቃቀም በተለይ ከጫት ጋር በተ ያያዘ ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር አብሮ ለመስራት እቅድ እንደነበር ግን ምንም መልስ ከዩኒቨርሲቲው ምሁራን አልተገኘም፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጥናት ለመስራት ሙያውም ዕድሉም አሉ፡፡ የጠለቀ ጥናት ቢያደርጉ ችግሮቹ ይለያሉ፡፡ ባለሙያዎች ስለአጠቃቀሙ እየዞሩ ቢያስተምሩም የሚያዳምጥ ሰው አልተገኘም፡፡ አንድ ሰው ቢሞትም በኬሚካል ምክንያት ነው አይባልም፡፡ አቶ አየሁ ከዚህ ጋር ተያይዞ ያጋጠማቸውን ሲያጫውቱን ‹‹በአንድ ወቅት ጓደኛችን በጣም ሳለና ለምን ደማችንን አንታይም ብለን ሆስፒታል ሄድን፡፡ መሳርያው ስለሌለ መታየት አልቻልንም፤ አዲስ አበባ ሂዱ አሉን፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ አንበጣ ልንረጭ ሰሜን ጎንደር ሄደን ታንከሩን እንዳዘልኩኝ ሲያንሸራትተኝ ወደቅኩ፡፡ ኬሚካሉ በሙሉ ጀርባዬ ላይ ፈሰሰ፤ ስትወድቂ ሲነካሽ ቅሪቱ አንቺ ላይ የሚፈጥረው ነገር አለ፡፡ ደሜን መታየት ፈልጌ ደሜ ውስጥ ይኖራል አይኖርም የሚለውን ለማወቅ መሳርያው ስለሌሉ መታየት አቃተኝ፡፡ መሳሪያው ስለሌለ የኬሚካሉ ጉዳት አይታወቅም፡፡ ባህር ዳር ውስጥ ከቱኃን ጋር ተያይዞ ያለው ርጭት ከባድ ነው፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በዚህ ዙሪ ያ ጥናት ቢያካሂድ ብዬ አስባለሁ፡፡ አንቺም ያገባኛል ብለሽ መምጣትሽን አደንቃለሁ፡፡ ጠንክሪና በጉዳዩ ዙሪያ ጥናት እንዲሰራ ማድረግ ይኖርብሻል፡፡ ዩኒቨርሲቲዎ ጥናት ሰርተው አደጋው ምን ያክል የሰፋ መሆኑን ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡ ህዝባችንም የችግሩ አንድ አካል በመሆኑ የበኩሉን እንዲወጣ ማድረግ አለብን፡፡»

የህክምና ተማሪ እንደመሆኔ መጠን በዚህ ዙሪያ መስራት አለብኝ ያልኩትን ጉዳይ በጽሁፍ ለማቅረብና የሚመለከታቸው አካላት የበለጠ ትኩረት እንዲሰጡት ለማድረግ የሚጠበቅብኝን ሃላፊነት ለመወጣት ተዘጋጅቻለሁ፡፡ የዚህ ጽሁፍ አላማም ይህን ስራ ለማገዝ ሲሆን ወደፊትም ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመሆን ለመስራት ወደኋላ የማያስብል ጉዳይ መሆኑን አጽዕኖት ለመስጠት ነው፡፡ ይህንን ጽሁፍ ለማዘጋጀት አቶ አየሁ ዘሪሁን እና በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የባዮኬሚስትሪ ትምህርት ክፍል መምህርና በጃፓን ሆኬዶ ዩኒቨርሲቲ ግራጁየት ስኩል ኦፍ ላይፍ ሳይንስ ተማሪ አብረሃ በጉዳዩ ዙሪያ አነጋግሬያቸው ለናይል ጋዜጣ አንባቢያን፣ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት መልዕክቱን እንሆ እላለሁ፡፡

ማላታየን ማለት በንክኪ (contact) ከሚገድሉ መድሃኒቶች አንዱ ሲሆን ተባዩን ለመግደል ከተባዩ ጋር መነካካት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም በርጭት ወቅት ወይንም በተረጨው ስፍራ ተባዮች በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ከመድሃኒቶች ጋር በመነካካት ሊፈጠር ይችላል፡፡

ፀረ-ተባይ ኬሚካል ማለት ማንኛውንም ተባይ የሚከላከል፣ የሚቆጣጠር፣ የሚያባርር ወይንም የሚገድል ማለት ነው፡፡ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠቃቀም ማለት ደግሞ ፀረ ተባይን በአንድ በተወሰነ ቦታ በዕጽዋት፣ በእንስሳት ወይንም በአፈር ላይ በማስቀመጥ፣ በመርጨት ወይንም በማትነን የተባይን ጉዳት ለመከላከል የምንጠቀምበት ዘዴ ነው፡፡ ፀረ-ተባይ ኬሚካልን የምንጠቀመው ሌሎች የመከላከያ ዘዴዎችን ተጠቅመን ተባዩን መቆጣጠር ሳንችል ስንቀር ነው፡፡

የፀረ-ተባይ ኬሚካል ጠቀሜታና ጉዳት

በመጀመሪያ የምንከላከለውን ተባይ በሚገባ በማወቅ ለተባዩ መከላከያ የሚሆነውን ትክክለኛውን ኬሚካል በመምረጥ ሰውንና እንስሳትን እንዲሁም አካባቢን በማይበክል መልኩ መጠቀም ይኖርብናል፡፡

ጠቀሜታ
ሌሎች መከላከያ ዘዴዎችን ማለትም ባህላዊ ወይንም የመከላከያ ዘዴዎችን ተጠቅመን የተባዩን ጉዳት መከላከል በማንችልበት ወቅት ፀረ-ተባይ ኬሚካል መጠቀም ወረርሺኙን በአፋጣኝ ለመቆጣጠር ያስችላል፡፡ የመከላከል ብቃቱ ከፍተኛ ስለሚሆን ጊዜን፣ ጉልበትን፣ የሰው ሃይል ፍላጎት ይቀንሳል፤ በቀላሉ የተዘጋጀውን ፀረ-ተባይ ኬሚካል በተፈለገ ጊዜ በአፋጣኝ ማግኘት ስለሚቻል የተባይ ጉዳትን በአፋጣኝ መግታት ያስችላል፤ ለአጠቃቀም ቀላልና ምቹ ነው /መመሪያዎችን በአግባቡ ከተከተልን/

ጉዳት
በሰው በእንስሳትና በአካባቢ ላይ ጉዳት ያደርሳል፤ ተባዩን በምንከላከልበት ወቅት የተባዩችን የተፈጥሮ ጠላቶች ጨምሮ ስለሚገድላቸው የተፈጥሮ ሚዛንን ያናጋል፤ በአንድ አካባቢ የተባይ ለውጥ እንዲመጣ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ ሰፋፊ ቅጠል ያላቸውን የአረም ዝርያዎች ባጠፋን ቁጥር ሌሎች አዳዲስ የሳር አረም ዝርያዎች እንዲተኩ እናደርጋለን፤ በተረጨው ተክል ስነ ህይወት ላይ በማቃጠል ወይንም አበባውን በማርገፍ ውስጣዊ አሰራሩን በማዛባትና እድገቱን በመግታት ጉዳት ያደርሳሉ፤ በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ሲውሉ ተባዩ ፀረ- ተባይ ኬሚካሉን የመቋቋም ባህሪ ያሳድሩና በቀጣይ የመከላከያ ወጭን ከፍ ያደርጋሉ፡፡

የፀረ-ተባይ ኬሚካል ዓይነቶች
ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በተለያዩ ዘዴዎች ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ በሚቆጣጠሩዋቸው የተባይ ዓይነቶች መሠረት ሲከፈሉ፡- ፀረ-ነፍሳት ተባይ፣ ፀረ-በሽታ፣ ፀረ-አረም፣ ፀረ-አይጥ ወዘተ. . በመባል ይጠራሉ፡፡

## ፀረ-ነፍሳት ተባይ መድሃኒቶች (insecticides)

ነፍሳት ተባይን ለመቆጣጠር ጥቅም ላይ የሚውሉ ሲሆኑ እንደ ንጥረ ነገር ይዘታቸው ልዩነት የተለያዩ ነፍሳት ተባዮችን ለመቆጣጠር የሚችሉ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ለምሳሌ-- ማላታይን፣ ኢንዶሰልፋን፣ ካርባሪል፣ ሳያፐርመትሪን፣ ዱርሰባን ወዘተ. . . በመባል ይታወቃሉ፡፡ የሚቆጣጠሩዋቸዉም ተባዮች


- ማላታዬን 50% -- የሚቆጣጠረው ተባይ ፌንጣ፣ ተምች. . . ወዘተ
- ኢንዶሶልፈን 35% የሚቆጣጠረው ተባይ ጓይ ትል.፣ቀይ የጤፍ ትል . ወዘተ
- አክቴሊክ 2% ሽርክት-- የሚቆጣጠረው ተባይ የጐተራ ተባዮች. . . ወዘተ
- ዳይሜቶየት 40% ኢሲ--
- የሚቆጣጠረው ተባይ ክሽክሽን፣ አንጥራ. .ወዘተ

## ፀረ-ተባይ ኬሚካል ስንጠቀም ማድረግ ያለብን ጥንቃቄዎች

በአንድ ወቅት የተከሰተን ተባይ ለመከላከል ፀረ-ተባይ መድሃኒት ከመጠቀማችን በፊት ሌሎች የመከላከያ ዘዴዎች (ባህላዊ፣ ስነህይወታዊ የመከላከያ ዘዴዎችን) መጠቀም ይኖርብናል፡፡ ተባዩን በእነዚህ ዘዴዎች ለመከላከል የማንችል ሲሆን ብቻ ነው ፀረ-ተባይ ኬሚካል መጠቀም የሚኖርብን፡፡ ስለሆነም ፀረ-ተባይ መጠቀም የግድ ካስፈለገ የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ማድረግ ያስፈልገናል፡፡



- ትክክለኛውን ፣ልናገኝ የምንችለዉንና አካባቢን የማይበክል ፀረ-ተባይ መምረጥ
- አስፈላጊ የመከላከያ ትጥቆችን ማሟላት
- በትክክለኛው መጠን ማዘጋጀት (Calibration)






ወደ ገጽ 15 ዞሯል

# From Fault-Finding to Empowering

continued from page 7

to the efforts of building a research culture of reflective practice.

- Offer a **thesis seminar** in which students and advisors engage in reflective research practice. In this arrangement, students from a number of different programs in related fields meet with a small group of advisors on a weekly basis. Students are expected to share regular updates about the development of their research proposals. The environment is one of mutual learning, curiosity, and support. Teachers ask questions to help students think more critically and more creatively about their frameworks and analysis. By the end of the seminar, advisors have ample evidence of the quality and originality of students' work. The work cannot be plagiarized, because advisors have seen it develop in the students' own words as early as the proposal writing phase. And this is the key point: quality is not "tested" at the defense, because the quality has been improved and demonstrated over time. Assessment of research quality becomes a continuous process. And then the defense becomes an affirmation of quality and a dialogue about the professional implications of the research – not a one-off (and frequently negative) judgment.

- Establish a university-wide **academic writing center**. This center could provide expert guidance to students and staff regarding specific issues to improve their academic writing. Such a center would assist postgraduate students and staff to prepare research articles for publication and review drafts prior to submission.
- Establish a university-wide **methodology workshop**. Staffed by experts in quantitative and qualitative methodologies, this workshop would function as an advising center to improve methodological rigor and relevance. Students – as well as staff – would be welcome to go to the center to get detailed feedback and advice on all aspects of methodology (from data collection to analysis). Similar to an academic writing center, the methodology workshop would also reduce advisors' burden by providing additional expertise in research methodology.

- **Establish minimum standards** for advisors to meet with students during the preparation of MA thesis and PhD dissertations. For example, students should be required to consult with advisors at least once per month (whether face to face, over email, or by phone) after completion of the research seminar described above. During these consultations, students would continue to provide regular updates on their progress and get detailed feedback on draft chapters.

- Advisors should convene a **"green light" meeting** with the student and examiners at least 3-4 weeks BEFORE a thesis/dissertation defense. In this meeting, there should be an in-depth discussion of any serious concerns that examiners may have about the research design, methodology, or presentation of data. Such a meeting can give the student and advisor time to address the concerns and for the examiners to give a "green light" for moving forward with defense. (Of course, if there is a "red light" then the student has more work to do, before the defense is held!) With a go-ahead signal from advisor and examiners, there can be greater attention paid to the professional significance of the work during the defense proceedings, rather than focusing on "fault finding". The defense can become an affirmation of students' good work, a culminating moment of pride in their research.

Of course, implementing these strategies requires extended discussion among advisors, postgraduate program coordinators, department heads, and the School of Graduate Studies—as well as with interested postgraduate students as it might challenge existing regulations. We encourage this kind of discussion, based on critical reflection about the challenges and limitations of the current research culture.

How can the university move beyond a culture of fault-finding? From our perspective, further dialogue about this question can strengthen the University's capacity to produce high-quality, innovative research. We believe it is possible to become a community that builds students' confidence, skill, and motivation for life-long professional inquiry. Isn't that the kind of outcome a premier research university aims to achieve?

# ማንነትን የሚያዋድቅና

ከገጽ 14 የዞረ

"ሁነኛ ተያዥ፣ ወይ የቤት ፕላንና ካርታ ወይ የመኪና ሊብሮ ያለዉ ተያዥ ካለሽ ምን አለ!" አለ መንከትከቱን ቀጥሎ፡፡ አልማዝ አስናቀን እራቱን ጋብዛ "በል በኋላ ምሽትሽት ሲል ና ዛሬ ለየት ያለ አራት ነዉ የምጋብዝህ፡፡ እንዲህ ያለ ጆግና በጣም እወዳለሁ፡፡ አደራ እንዳትቀር አደራ" አለችዉ፡፡ አስናቀ ገና ከበሩ ሲወጣ ወ/ሮ ሰላማዊት ምስኗ ድንቅ እያለ አስቸገረችዉ መቀሌ ልማት ሰራተኛ እያለ የማትደፈር የምትመስለዉ ቆንጆ ወ/ሮ ሙሉ ፈግግታና አካላዊ ተራክቦ በአይነ ህሊናዉ እየተመላለሰ ወጣ ፡፡

"እኔ ቁሜ ተቀምጬ ጆግና ነዉ እምወደዉ፡፡ እንኳን የወንድ የሴት ጆግና ደስ ይለኛል" እያለች መሸት ባለ ቁጥር ቤቷን እየዘጉ ያሳለፉት የስርቆት ፍቅር ታወሰዉና የወንዳወንድ ሰዉነቱ ሞቆ የሱሪዉ መራጠብ ለራሱ ገረመዉና "ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ" አሉ፡፡ ሆ..ሆ..ብሎ ተጓዙ ሰአቱ መሸትሸት እስኪል ከቀበሌ 6 ጎራ ብሎ ቢራዉንና ሁለት መለኪያ አረቄዉን ጋር ተለብሶ ቆየ፡፡

የመጠጥ ቤቱ ቴሌቬዥርን የአራት ሰዓት ዜና ሲል ትዉስ አለዉ፡፡ ሂሳቡን ከፍሎ ወደ ማደርያ ቤቱ ሄዶ የክት ልብሱን ለብሶ፣ ጋቢዉን ድርቦና ከዘራ ይዞ ወደ አልሚ ቤት ከተፍ አለ፡፡ ልጆቹን አስተናግዱ ብላ ገንዘብ ተቀባይ የሆነችዉን ጠቅሳ አለባበሱና ንቃቱ ገርሟት ወደ ምኝታ ክፍሏ ይዛዉ ገባች፡፡ "ወይ ቅዱስ ሚካኤል! ደስ የምትል እለተ ማክሰኞ!" በማለት ፈጣሪዋን አመሰገነች አስናቀን ባኞ ቤት አስገብታ እንደስንዴ ፈትጋ አጠበችዉ ና በል እኔንም እዚያዉ እጠበኝ፡፡ ፆታዊ ዝምድናቸዉን አጠናክረዉ እንደጨረሱ ከከረጢቱ አዉጥቶ የሰጣትን 250ሺህ ብር ያለ እማኝና ተያዥ ተገርማ ተቀበለችዉ፡፡ "ግን ተምረሃል ልበል?" አይ እርሱን ሌላ ቀን ብሏት ብዙ ተጨዋወቱ፡፡ "አንድ ቃል ግቢልኝ?" አላት፡፡ "እንዴት ብዬ አስኔ …" ብላ ሳትጨርስ በኋላ እንዳትከጅኝ!" ሲል "እረ ቅዱስ ሚካኤል አንተ እኔ እኮ ማተብ ያለኝ ክርስቲያን ነኝ በስመአብ! እንኳ ለወረት አበቃኸኝ እንጂ ሁለት አመት አይቆይ ሰርቼ ነዉ የምመልስልህ ….አብሽር! … ግን አንተም ቃል ግባልኝ፣ አልሚን እንዲህ አደረኳት … ይኸን ስትል ብሰማ …." "እረ አልልም! ግን ቢያንስ በሳምንት ….ያዉ ነዉ!" ብሎ የደረቷን ፍሬ ተመለከተና ሳቀ፡፡ ደስታና ክብር በተሰማዉ ስሜት አይነት አገላለፅ "አብሽር ለሱ የሞባይል ስልክ ተለዋወጥን አይደል! እኔዉ እራሴ እያሰብኩ እጠራሃለዉ፡፡ ግን ምስጢር ምስጢር ነዉ ….አይደል!" አለችው፡፡

በየሳምንቱ እኔና ስመኝዉ ወደ አልሚ ቤት መጓዝ ጀምረናል፡፡ መንገድ ላይ ሞላ ያለ ደልደላ ሰዉነት ያለዉ ባለ ፍዝ ቆቡ ብቻዉን እያወጋና እየተንገዳገደ በመጓዝ ላይ ነዉ፡፡ "አንገቴ ስር ዉሽቅ ብላ ስትስመኝ ልቤ እንደቅቤ ቅልጥ ያለዉ…..ግን ምን ነካኝ?" እያለ ብቻዉን ሚሊኒየም ካፌን አልፎ ወደ ጊዮርጊስ መንገድ ቀጠለ፡፡

እኔና ስሜ እየተንቀሳቀስን አየነዉና ቆቡን ዛሬ ላይ በግራ እጁ ይዟታል፡፡ ብቻዉን መነጋገሩን ቀጥሏል፡፡ ስሜ አስናቀን ሲያይና ድርጊቱን ሲያጤን ወዲያዉኑ የዶክተር ገድፍ ጌታቸዉን እናት ወ/ሮ ዘዉዴን አስታወሰ፡፡ ''ሶል በሚቀጥለዉ ሳምንት እኮ ወደ ወገዳ እሄዳለዉ! አንድ ማህበራዊና ጥናታዊ ስራ እሰራለሁ ብዬህ የለ?" አለኝና ትኩር ብሎ መልሴን ተጠባበቀ፡፡

"የት ነዉ ወገዳ ባክህ?" አልኩት፡፡ እኔም በየተራ የስሜን አይን አይኑን እያየሁ፡፡ "ስማዳ ማለቴ ነዉ፡፡ እዚያ የተመረጡ 11 ቀበሌዎች አሉ ባለፈዉ አንዳቤት፣ አርብ ገበያና አንበሳሜን አካባቢ ሠርተናል ብየህ የለ?" ብሎ አስታወሰኝና "ከጥናት ቡዱኑ ጋር ነዉ የምሄደዉ በዚያዉም የወ/ሮ ዘዉዴ ሁኔታ የአዕምሮ ችግርም ሆነ ወይም ሌላ ከእርሳቸዉ ወይም ከቤተሰባቸዉ አረጋግጬ የሚቻለኝን መርዳት አለብኝ፡፡" ሲል በተመስጦ እያወራኝ እኔም እርሱ ከራሱ አልፎ ለሰዉ መኖሩ እየገረመኝ "በል ግዜ ካለህ ጥሩ ነዉ" ብዬ ስጀምር ወሬዬን ስያስጨርሰኝ "አይህ በልመና ሥራ አንድ ሰዉ በሆነ ችግር ምክንያት ለአንድ ቀን እንኳ ቢገባበት ጣዕም ጣዕም ይለዉና ሱስ ሆኖበት ከመስኩ አይወጣም፡፡ ድንገት እርሳቸዉም … " ብሎ ሳይጨርስ ሁለታችንንም አንዳች የሚሰቀጥጥ የአደጋ ድምፅ አቋረጠን፡፡

ድንገት ፊት ለፊት አንዲት የዘመኑ ሞዴል መኪና ከባጃጅ ጋር ተጋጭታ ከመንገድ በመወጣት ከመንገዱ ጠርዝ ያሉትን ሌሎች ሁለት ሰዎችን ጭምር ገጭታ አካባቢዉን አናወጠችዉ፡፡ ጩኸቱ የኢትዮጵያዉያን የተለመደ ቀና የመደጋገፍና ህይወት የማትረፍ ሩጫዉ የደመቀ ገበያ አይነት ሆኗል፡፡ ፖሊስ፣ ሌላ ሌላዉ ሰዉ፣ አምቡላንስ … እኛም ያለ ፕሮግራማችን አብረን ወደ ፈለገ ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል ነጎድን፡፡

ይቀጥላል!

# የጉዞ ማስታወሻ

ከገጽ 9 የዞረ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንፎርሜሽንና ስትራቴጁክ ኮሚዩኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ የብዕር ማስቀመጫ፣ ቲሸርት፣ የእጅ ሸዋልያ፣ የዶክመንት መያዣ ቦርሳና የወንዶች የኪስ ቦርሳ በስጦታ አበርክተው ዩኒቨርሲቲው ስለ ህዳሴው ግድብ ልዩ ትኩረት እንዳለውና ሁሉም ጉብኝ በተጨባጭ የሚሰራውን ሁሉ በማየት ኢትዮጵያዊ ኩራት ሊሰማው እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡ እንጅነር ስመኘውም የዩኒቨርሲቲው ልኡካን በተለያየ ቡድን በተደጋጋሚ እየመጣ እንደሚጐበኘውና ሁሉም ተጓዥ አንድ አይነት የዩኒቨርሲቲው ቲሸርት ለብሶ መታየቱ አንድነታችሁን ስለሚገልፅ ለወደፊትም እጅ ለእጅ ተያይዘን እንደምንጨርሰው አሳስበው ለተደረገው ስጦታም ታላቅ ምስጋና አቅርበው ከሳቸው ጋር ተለያይተን ሁሉም በየመኪናው እንዲገባ ስለተነገረው ምንም እንኳ ወቅቱ ክረምት ቢሆንም ፀሀዩ ግን ከበጋው ወራት በበለጠ መልኩ ያቃጥል ስለነበር ከገለፃው በኋላ ሁሉም እየተሯሯጠ በየመኪናው ገባና ወደሚጐበኘው ቦታ ሄደን «ማየት ማመን ነው» እንደተባለው በፅንሰ ሀሳብ ከሥራ አስኪያጁ የተገለፀልንን በተግባር አይተን በአስጐብኝዎች አማካኝነት ገለፃ ከተደረልን በኋላ ተመልሰን ወደ መኪናዎቻችን ገብተን እንደገና ሌላ ቦታ እየጐበኘን ከኢንጅነር ስመኘው ጋር በቡድን በቡድን በመከፋፈል የፎቶ ግራፍ ፕሮግራም ከተከናወነ በኋላ ቦታው እጅግ ሰፊና በአይን የማይደረስ ስለሆነ አንዱን ትእይንት እንደጨረስን ወደ ሌላው ለመሄድ የግድ በመኪና ስለሆነ አሁንም ተሳፈርንና ወደ ምሳ ቦታ ሄድን፡፡ እንግዲህ ሌሊቱንም ቀኑንም በጉዞ የዋለን ሰው እንዴት ይበላል ብሎ ማሰብ «ለቀባሪ ማርዳት አይነት ነገር ነው የሚሆነው፡፡» ሰልፉ አሰልች ቢሆንም የሆድ ነገር ስለሆነ ተሰልፈን ተራ ሲደርሰን ገብተን ስንመገብ እኔን ያስገረመኝ ነገር እዚያ ቦታ ላይ ያልጠበኩት «የቡፌ ምግብ» አቅርቦትና የማቅረቢያ ቁሳቁሶች እጅግ በጣም ዘመናዊ መሆናቸው እንዲሁም የምግብ አዳራሹ ስፋትና የወንበሩ ብዛት፣ «ፍላት ስክሪን ቴሌቪዥን» እና በየቦታው ላይ ተሰቅለው ለአፍታም ቢሆን እንኳ ትንሽ ቀዝቀዝ የሚያደርጉትን የግድግዳ ኤሲ (ዘመናዊ የአየር ማቀዝቀዣ) በየኮሪደሩ ተሰቅለው እየበላችሁ ተዝናኑ የሚሉትን ተመልክቼ እጅግ በጣም አስገራሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

እኛም የቻልነውን ያህል ተመገብንና ስንወጣ መፀዳጃ ቤት ያለው ወረፋ ከመጀመሪያው ሰልፍ የባሰ ስለነበር እንደምንም ሁሉን ነገር አግኝተን ሰዓቱ በጣም ስለመሸ መንገድ ላይ እንቸገራለን እባካችሁ ፍጠኑ የሚለው ማሳሰቢያ በየደቂቃው ስለሚነገር ቶሎ እንደ ጨረስን በየመኪኖቻችን ገብተን ጉዞ ቁጥር 3 ወደ ግልገል በለስ ለመመለስ 8፡20 ላይ ተጀመረ፡፡ ከዚህ በኋላ ውድድሩ የማራቶን አይነት ሆነ ምክንያቱም በጣም ሳይመሽ ለመድረስ የቻለ መኪና ማብረር እንደሚችል ስለተነገረ መጠባበቅ ሣየኖር ስንጓዝ በኋላ የቀሩት ሁለቱ መኪናዎች የአንደኛው ጐማ ቀንሶበት አንደኛውን ጠብቀኝ በማለት ወደኋላ ዘግይተው እኛ ከገባን በግምት ከሁለት ሰዓት ቆይታ በኋላ አምሽተው መጡና እራት እንደነገሩ ቀማምሰን የቻለ ማምሸት፣ መጠጣትና መዝናናት እንደሚችል ቢነገርም እኛ ድካሙ ስለተጫጫነን ሄደን ተኛን፡፡ የጧቱ ጉዞ ስንት ሰዓት እንደሆነ ኮሚቴዎችን ስንጠይቅ ሁለት ሰዓት ላይ ነው ስለተባለ ያለ የሌለ እንቅልፍና ድካም ጨርሰን ሲነጋ አንድ ሰዓት ላይ ተነስተን ወደ መኪናዎቻችን ስንሄድ ሁሉም በድካም ያወጣውን ኃይል ለመመለስ ይመስላል በየቦታው ተሰግስጐ ቁርስ አይሉት ምሳ በሀይለኛው ይበላል፡፡ የኔ ጓደኞችም እንብላ አሉኝ እኔ ግን ቀኑ ዕለተ ሰንበት በመሆኑ ከምበላ ይልቅ ቤተክርስቲያን ብሄድ ይሻለኛል ብዬ ስሄድ ጓደኛዬን ለመሄድ እንቅስቃሴ ሲኖር ደውይልኝ ብያት ሄጀ ለካ እሷ ደግሞ ሌላ እቃ ልትገዛ ከመኪናዎች ርቃ ኖሯል! ስትደርስ መኪናዎቹ ጉዞ ሊጀምሩ ሲሉ እኔ ደግሞ ሳልመጣ በጣም ተደናግጣ ደውላ በቃ መኪናው ትቶሽ እየሄደ ነው አለችኝ፡፡ እኔ ደግሞ እሷን አምኘ እንዴት እስከሚሄድ ዝም አለችኝ ብዬ እግሬ አውጭኝ የአካባቢው ሰው በግርምት እያየኝ ያለ የሌለ ኃይሌን ተጠቅሜ ስሮጥ ከርቀት አይተውኝ ሌሎችም መኪናውን አስቁመው እነሱም ወርደው እንድደርስበት አደረጉኝና አብሬ ጉዞ አራትን የመጨረሻውን ጉዞ ወደ ባሕር ዳር ጀመርኩት፡፡ ስንመለስ የአገራችንን ሰማይ ለማየት ጉጉት ይዞን ስለነበር አስቸጋሪው መንገድም ሣይታወቀን ቶሎ ቻግኒ ከዚያም ኮሶበር፣ ዳንግላ… እያልን እንደመኪናዎች ፍጥነት ከ5፡45 እስከ 7፡00 ሰዓት ድረስ ባሕር ዳር ከተማ ደረስን፡፡

# ማንነትን የሚያዋድቅና ሞራልን የሚገድል ንግድ

## (ሃይ ባይ የሌለበት ግብርና ኪሣራ የለሽ ንግድ!)

## ክፍል አንድ

በመተሳሰብ ክብሩ

የፀሐዩ ግለት አያድርስ ነዉ! ቀጠሮ አክባሪዉ ጓደኛዬ ያለወትሮዉ አስራ አምስት ደቂቃ ዘገዩ እንኳንስ አርፍዶ ነዉና ለቀጠሮ ሰአት መድረሻ ''ቀጠሮአችን እንደተከበረ ነዉ ብዬ አምናለሁ ወደ ቦታዉ እየደረስኩ ነዉ አመሰግናለሁ'' ፡፡ የሚለዉ ድምፁ ርቋል ፡፡ አስራ ስምንት ደቂቃ እንዳለፈ "ምነዉ ጌታዬ?" ስል ሀሎ አልኩ፡፡"በሩ ላይ ቆሜአለሁ፤ ከመጣሁም ቆየሁ አንድ ነገር እንዳያልፈኝ ነበር፡፡የይቅርታ ወሬ አሚልቼ ሳምጣልህ ብዬ ነዉ" ብሎ 2ደቂቃ ጨምሮበት ሁሌ በሚያስቀናዉ ፈገግታዉ ታጅቦ ወደ ጎንጬ ቀረበ ፡፡

አያቴ ነፍሷን ይማረዉና! ወዳጆቿን በጎንጮቿ በተለየ ቤተሰባዊ አሳሳሟ ነበር አክብሮታዊ ፍቅሯን የምትገልፅላቸዉና ሁሌ ስንሳሳም አሳሳሙ ቁርጥ አያቴን በመሆኑ ከጓደኝነት የበለጠ ዉድድድ….. አድርጌ ብቻ ምን አለፋችሁ! በጣም እወደዋለሁ ፡፡

"ብዙ ቆየሁብህ አይደል? ይቅርታ! የቆየሁበትን ላወራህ ነዉ'' አለኝ እየተፍለቀለቀ፡፡

አንድ ሽማግሌ አይሏቸዉ ወጣት ቆባቸዉን አይናቸዉን እንዲሸፍንላቸዉ አድርገዉ ዝቅ ያደረጉ ናቸዉ፡፡ አለባበሳቸዉም ዘባተሎ ነዉ፡፡ ''ዋናዋ የሉም? እርሳቸዉ ነበሩ ሳያሳስቱ የሚዘረዝሩልኝ፤ ርሐቤንም ያዉቁታል "አሏት ለአስተናጋጇ፡፡ "ያዉ መጣች" አለች እና ወደ ስራዋ ተጣድፋ ሄደች፡፡

የሻይ ቡናና ምግብ ቤቱ ባለቤት ወ/ሮ አልማዝ ይነጠፏልሽ "ግቡ፣ ግቡ! ምነዉ አረፈዱ? ስንት ደንበኛ ተቸገረብኝ መሰለዎት? ቶሎ ያምጡት ብላ ከረጢቱን ተቀበለቻቸዉና ባንኮኒዉ ላይ ዘረገፈችዉ ፡፡

ዘባተሏቸዉን አይቼ አንቱ አልኩ እንጂ ሰዉየዉ አንድስ የሚያክል ጎረምሳ ነዉ፡፡ አልማዝ ይነጠፋልሽ ትቆጣጥራለች ሳንቲሞቹን …. ሰዉየዉም አይኑን እጆቿ ጣቶችና ሳንቲሞቹ ላይ ተክሏል፡፡ 2ቱ የተቀመጡበት የማስተናገጃ ጠረጴዛ ተደበደበ፤ ''ይሺ፣ይሺ የት ናችሁ ልጆች! ምነዉ እቴ!'' እንዳለች ሁለት አስተናጋጆች ወደጥሪዉ ሄደዉ ማስተናገዱን ተያይዘዉታል፡፡

"ስንት ነበር ያልኮዎት? "አለች አልማዝ ይነጠፋልሽ……" ሁለት መቶ ሰላሳ ሰባት ነዉ እርሱ የተቆጠረዉ" አለ ሰዉዬዉ፡፡ አዎ ልጄ! አለችና አንድ መቶ አርባ ሶስት ብር ጨመረችበትና ሶስት መቶ ሰማኒያ ብር ነዉ ጠቅላላ፡፡ የሚገርም ነዉ ይህን ሰሞን ቀንቶሃል፡፡ ከሦስት መቶ ምንም አልቀነስክም" አለችዉና ከት ከት ብላ ሣቀች፡፡ "እረ ዛሬስ ህዳር ሚካኤል የአመቱ አይደል! እርሱን ይስጡኝና ሌላ ከረጢት አለኝ አለና መዘዝ አድርጎ በጥንቃቄ ጉድለት እንደሚሰበር ብርጭቆ በሁለት እጆቹ ደግፎ አስቀመጠዉ፡፡

ወ/ሮ አልማዝ ይነጠፍልሽ 380ዉን ብር ቆጥራ ሰጠችዉና ''ቆይ ይሄ ወደ ዉስጥ ይግባ'' ብላ በሰፊ የፕላስቲክ ሣህን ዉስጥ ጨመረችዉና ሣጥኑን መልሳ የሌላዉን ከረጢት ሳንቲም ከመቁጠሪያዉ ባንኮኒ ላይ ሆጨጨጨጨጨጨጭ… አደረገችዉ፡፡

ሃምሳና፣ ስሙኒዎችን፤ ባለ አንድ፣ አስርና አምስት ብሮችን በመለየት ተያይዘዋለች … አቋርጣም "አይ ዛሬ ያለፈበት የሎተሪ ትኬትም ሰጡህ መሰለኝ? አይ የኛ ነገር አለመስጠት አይሻልም? ስትል፡፡

ባለቆቡ ዲሪቶዉን በቀኝ እጁ ከፍ አደረገና በግራ እጅም ቆቡን እያስተካከለ ''አይደለም እሜቴ ባልና ሚስቱና ልጃቸዉ ናት መሰለኝ ሦስቱም አንዳንድ ወረቀት ጣሉልኝ ትዝ አለኝ:: ሎተሪ አይደለም ዶላር ፣ዶ……ላ…..ር ነዉ'' አለና ''ይስጡኝ እርሱን'' ብሎ እጁን ሰደደ፡፡ቀና ብላ እያየችዉ፡፡

''አዎ ልጄ! አምስትአምስት ዶላር ነዉ እርሱም ይኸዉ'' ከዘረዘሩ ይዘርዝሩት ሌላምአለኝ" አለ ሱሪዉን ዝቅ አድርጎ ከዉስጡ ሱሪዉ በላስቲክና በሲር ክር አጥብቆ ጠቅልሎ የሰፋዉን 25 ዶላር በመምዘዝ ''ይቆይ ፣ይኸ ይቆይ ለብቻዉ'' ብሎ በቀኝ እጁ ይዞ ሳንቲሙ ላይ አፈጠጠ፡፡ ምራቋን ዋጥ አደረገችና ልጄ!"በለስ ቀንቶሃል! ሚካኤል ዛሬ ሳንተ ሆኖሃል ..ሆ..ሆ!" ከተገረመች በኃላ አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ብር ሳንቲም ቆጥራ ጨረሰችና የባንኮኒዉን የሒሳብ ሣጥን ከፍታ ስትሰጠዉ "ጥቅል አንድ መቶ ሃምሳ ያርጉት አንዱን ብር ነገ አመጣለሁ፡፡ አለበዚያም እርሶዎ ይዘክሩኝ" አለና አይን፤ አይኗን ተመለከተ በተራዉ፡፡

"እሽ ልጄ! እርሱስ አያጣላንም፣ ይኸንስ በስንት ነዉ የምትዘረዝረዉ?" ዶላሩን በእጇ ይዛ "ወይ አምላኬ! እኔም ይኸን ይኸንን የፍሬ ግብር ታክስ፣ ባት፣ የሠራተኞች ደመወዝ፣ ቤት ኪራይ … ከምል በልመናዉ ልሰማራ ይሆን? የሚገርም እኮ ነዉ!" አለች፡፡

"እረ ምን በወጣዎ! ይኸንን ለማግኘት ከዕድል ባሻገር ከዋዜማዉ ጀምሮ ከቀኑ ሰባት ሰአት ላይ በቦታዉ ተገኝቶ ወረፋ ይያዛል፡፡ ለዘበኛዉ ጉቦ አለ፣ እረ ምን ቅጡ! ለርስዎስ አይመችም፡፡" አለ ባለቀዩ ፍዝቆቡ ለማኝና ዘርዛሪ….. ''አበስኩ ገበርኩ! እረ ዉሸቴን ነዉ ፈጣሪዬ! ግን በእናተ ላይ መንግስት እጁን ያልቀሰረዉ ለምንድን ነዉ፡፡ ነዉ? ግብርና ኪሳራ የለሽ አዋጭ ቢዝነስ መሆኑን አላወቀም? የሚገርም እኮነዉ!!" አለችና እየሳቀች በኩል የደመቁ አይኖቿን ወደ እኛ እየወረወረች የአዳንቁልኝ ጥሪ አይነት እያሰማች "አይገርምም ግን? ምን ልበል ገርሞኝ እኮ ነዉ አኗኗሯአችን? ብላ ሣቋን ነሰነሰችዉ፡፡

"በቃ በሃያ ሒሳብ ይዘርዝሩት" አለ ባለ ፍዝ ቆቡ፡፡ ወ/ሮ አልማዝ ያለጥርጥር አንድ ባለ ሐያ አምስት ሊትር የሚይዝ ጀሪካን ፈሳሽ ነገር ወይም 50 ኪሎ ዕቃ ማፈናጠጥ የሚችለዉን ጀርባዋንና ዳሌዋን እያወናጨፈች ወደኛ ጠረጴዛ መጣችና ባይሆን "ፎርጁዱ እንዳይሆን እዩት እስቲ" አለችን፡፡

ጓደኛዬ ድንገት "ይቅርታ! መጣሁ" ብሎ ምንጥቅ ብሎ ወደ በሩ ወጣ፡፡ በር ላይ የአንድ የህክምና ዶክተር ጓደኛዉ እናት፤ ሁሌ ስማዳ ሲሄዱ ሲያርፍባቸዉ የነበረ (ዛሬ ላይ ሞቷል ዶክተሩ) ጠይም ሙሉ ፈገግታ ያላቸዉ እረ በሞቴ? ብሉ እንጂ እያሉ የሚያስተናግዱት ወ/ሮ ናቸዉ፤ ለዛዉም አንቱ የተባሉ ቤትና ትዳር ያላቸዉ፡፡

"ለጠበል አንዳሳ መጥቼ ቆይቼ ነዉ፤ መሣፈሪያ እርዱኝ" ብለዉ ሲለምኑ ትልቅ ሰዉ መሆናቸዉን አይቶ ብቻ ወደ ምግብ ቤቱ ከመግባቱ በፊት አስር ብር ሰጥቷቸዉ አልፋል ግን ልብ አላላቸዉም ነበር፡፡ ምግብ ቤቱ ፊት ለፊት ለአንድ ባለ ታክሲ ረዳት የ20ብር ሳንቲም ዘርዝረዉለት "ይመችሽ ደንበኛ እንሆናለን" ብሏቸዉ ሩጦ ታክሲ ዉስጥ ገባ፡፡ ሒሳባቸዉን ቢሰጣቸዉም መሮጡ ግራ አጋብቷቸዉ የራሳቸዉን የወሰደባቸዉ መሰላቸዉና

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

# ፍናፍንት...

ከገጽ 10 የዞረ

መስኩን አጨቅይቶታል፡፡ የሹሜ እጇን ልካ መሬት ላይ እተዘረረው ሰው ደረት ላይ አሳርፋ ቆየችና “ወይኔ” አለች የማጓራት ያህል ድምጧ ጎርንኖ፡፡ ወዲያው እልህ እየተናነቀ ይሰብቃት ጀመር፡፡ የያዘችውን አጭር ምንሽር በግራ እጇ አንጠልጥላ እየተቅበጠበጠች በአይኗ ሰው ትፈልግ ጀመር፡፡

“ማነው የተበላሸው ጎበዝ?” አለ አንዱ ወሬ የጠማው ገና ሬሳውን ከመመልከቱ፡፡

“ቆጨው” መለሰለት ሌላው

“ቆጨው ቆጨው?” ጠየቀ የመጀመሪያው

“ቆጨው ያቶ ዘርጋው ልጅ ነዋ!” መለሰ ሌላው

“እንዴ እንዴ ቆጨው ይሄ ሃብትሽን ያጨው!?”

“አጭቷት ነበር እንዴ?”

“አልሰሜን ግባ በለው! ይሄማ አገር ያወቀው ጣይ የሞቀው አይደል እንዴ! እንዴት አላወክም?” አለ፡፡

“ወይኔ ልጄን. . . ወይኔ ልጄን. . . ማነው ጠላቴ? ማነው ጉድ ያረገኝ?” የሚል የለቅሶ ድምፅ ሲሰሙ ሁሉም ዞሩ፡፡ የሚች አባት አቶ ዘርጋው የልጃቸውን አስክሬን የሙጥኝ ብለው ያለቅሳሉ፡፡ ሁሉም ተረባርበው ካስክሬኑ ላይ አንስተው ደጋግፈው አቋሟቸው፡፡

የሚች ታላቅ ወንድም ሸዋን ግዛው ፈረስ ላይ ከተባለው ኮረብታ እየተንደረደረ መጥቶ ሰው መሃል ሲገባ ወንድሙን ተዘቅዝቆ ከጭንቅላቱ ደም ሲፈስ ተመለከተው፡፡ ሰው ሁሉ አቦዳደኑንና የዱላ አያያዙን ሲመለከት ምን ሊፈጥር ይሆን በሚል ግምት ፀጥ ብሎ ይመለከተው ጀመር፡፡ ሸዋንግዛው ሰውነቱ በልህ እየተወጣጠረ

“ዘራፍ

ዘራፍ አካኪ ዘራፍ

ዘራፍ ሸዋን ግዛው

የዘርጋው ፍሬ የዘርጋው ግልገል

ጠላት አሳዶ አባሮ ሚገል

እናቱ ሞታ ያደገው ባባት

እንደ ቀትር ጅን ይመታል አናት

ዘራፍ ዘራፍ ዘራፍ. . .”

ብሎ ፎክሮ ዱላውን ጣለና የወንድሙን አስክሬን ከግራ ወደ ቀኝ ከቀኝ ወደ ግራ መልሶ ከግራ ወደ ቀኝ ዘለለና አይኑን ወንድሙ አስክሬን ላይ ተክሎ “ወንድማለም. . .” አለ አይኑን ከሞላው እንባ እየተናነቀ፡፡ “እንግዲህ ወንድሜ አይደለህም፡፡ ከንግዲህ ፈጥሞ ገንዘብ አቶነኝም፡፡ ግን ጠላቶችህ ጠላቶቼ ናቸውና ደምክን እምመልሰው እኔ ነኝ፡፡” ብሎ ዘወር ሲል እንዳይላሉ ከዘራውን ተመርኩዞ ቆሞ አየው፡፡ ከከበቡት ሰዎች ሁሉ የሱ ከዘራ ጥሩ ስለመሰለው ከጁላይ ነጠቅ አርጎት ሊሄድ ሲል “ጎበዝ ዳኝነት በህግ ነው” አለ የቀበሌው ሊቀመንበር ክላሹን ዘቅዝቆ እንዳነገተ እየተብቃቃ፡፡

የሹሜ የያዘችውን አጭር ምንሽር ወደ ግራ እጇ አዙራ ሊቀመንበሩ የተሸከመውን መሳሪያ በቀኟ አፈፍ አደረገችው፡፡ መሳሪያውን እንዳይነጠቅ ሸሸት ሲል የክላሹ ማንገቻ ተበጥሶ መሳሪያው የሹሜ እጅ ላይ አረፈ፡፡

“ና እንካ ይሄ ይሻላል” አለች ወደ ሸዋንግዛው ዞራ፡፡ አዝላ አጫውታ ባሳደገችው ሸዋንግዛው ቆራጥነት ልቧ በደስታ ቢሞላም የባሏ ከዘራ መነጠቅ እያንገበገባት፡፡

ሸዋንግዛው የያዘውን ከዘራ ጥሎ ከየሹሜ እጅ መሳሪያውን ተቀበለ፡፡ መሳሪያውን የተነጠቀው ሊቀመንበር “በህግ አምላክ እናንተ ሰዎች ህግ ይግዛችሁ!” እያለ እንደ እብድ ብቻውን ይለፈልፍ ጀመር፡፡ መጠጋትና መሳሪያውን ማስመለስ ግን አልደፈረም፡፡

ሸዋንግዛው “ባለወልድን ያላችሁ የወንድሜን እሬሳ አንሱልኝ፤ መሰረት ደግሞ ተከተለኝ” ብሎ መሳሪያውን አቀባበለና ሁለጥ ጥይት አከታትሎ ወደሰማይ ከተኮሰ በኋላ ማንንም ሳይጠብቅ ቁልቁል ተፈተለከ፡፡

መሰረት ሲከተለው የሹሜም ቁልቁል ተንደረደረች፡፡ ብዙዎች የሹሜን “ተመለሽ ወንዶቹ ይበቃሉ” ሊሉ ከቃጡ በኋላ እሺ እንደማትላቸው ስለሚያውቁ አፍ ከማጥፋት ብለው ዝም አሉ፡፡

የሹሜ ከልጅነቷ ጀምሮ ባካባቢያቸው ማንም ይሙት ማ ተንደርድራ ሄዳ ገዳይን ካልገደልኩ የምትል ሴት ናት፡፡ ካሁን በፊት ካንዴም ሁለት ሶስቴ ባካባቢያቸው ሰው ገሎ ያመለጠን ወንበዴ አባራ ይዛ ለህግ ሰጥታለች፡፡

አንድ ቀን ከሌላ አካባቢ የመጣ ሰው አንድ ያካባቢያቸውን ሰው ገሎ ሊያመልጥ ሲል የባሏን አጭር ምንሽር አውርዳ መንገድ አሳብራ ቀድማው ከመንገዱ ላይ ቆመችና አላሳልፍ ስትለው ገዳይ ወደሷም ይተኩስ ጀመር፡፡ የሹሜም ምሽግ ይዛ ስትታኮስ ግራ እጇን ተመትታ ወደቀች፡፡

ገዳይ ሁለተኛ ሰው ጣልኩ ብሎ እየፎከረ መሳሪያዋን ሊገፍ ሲመጣ እወደቀችበት መሳሪያዋን አመቻችታ ትተኩስና እጁን መታችው፡፡ ገዳይ መሳሪያው ከጁ ሲወድቅ ድጋሚ ትተኩስና እግሩን ስትመታው ይወድቃል፡፡ እወደቀበት ባካባቢው ታጣቂዎች ተይዞ ወደ መሃል ሜዳ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰደ፡፡ እሷንም አፋፍሰው መሃ ልሜዳ አጠቃላይ ሆስፒታል ይወስዱና ያሳክሚታል፡፡ የተመታችበት ጥይት ግን አጥንቷን ሳትነካ ስጋ ለስጋ አልፋ ስለነበር የከፋ ጉዳት አልደረሰባትም፡፡

ሰዎችም የባሏን ፍራትና የሷን ጀግንነት ይታዘቡና “እሷን ነበር እንጂ ሱሪ ማስታጠቅ፡፡ እንደው ምን ብትል ይሄን ቦቅቧቃ አገባችው” ይላሉ፡፡ ዛሬ ግን የሞተው እንደ ካሁን ቀደሙ ያካባቢዋ ልጅ አይደለም፡፡ አዝላ እሹሩሩ እያለች ያሳደገችው ያጓቷ ልጅ ነውና ጥቃቱ ጥቃቷ ነው፡፡

ይቀጥላል!

# ማንነትን የሚያዋድቅና

ከገጽ 13 የዞረ

“አይ ጉድ ሞጭልፎኝ ሄደ፡፡ እረ ያዙልኝ!” ሲሉ ጓደኛዬ ቀና ብሎ አይቶ “ምንም አልወሰደብዎም“ አለና ሲያስተዉላቸዉ ደንግጦ “እማማ ዘዉዴ ምነዉ?“ ሲል እርሳቸዉም በተራቸዉ አዩትና ደንግጠዉ ነጠላቸዉን እያረገፉ ዘንቢላቸዉንና ምርኩዛቸዉን ይዘዉ ጥለዉት ላጥ አሉ፡፡ ለአፍታም ዘወር አላሉም፡፡ “እንዴ?” ብሎ ፈዞ ቆመ፡፡ አንዷት ተማሪዉ ስታልፍ አየችዉና ‘‘ሃይ ቲቸር’’ ብላ ከሃሳቡ መለሰችዉ፡፡ ከርሷ ጋር ጥቂት አወራርተዉ ስልክ ተለዋዉጠዉ ተለያዩና በጉዳዩ ተገርሞ ነበር የተመለሰዉ፡፡ እያለ አልማዝ ያቀረበችዉን ዶላር አየና ‘‘ዘንድሮስ ለምንዛሬ በአየህ በፍለጋ የሚሳደደዉ ዶላር በለማኝ እጅ መዋል ጀመረ እንዴ’’ አለና ወደኔ ዞር አለ፡፡ አልማዝ በደንበኛ አቀባበሏ፤ በፈጣን መስተንግዶዋና ለጋስ ፈገግታዋ ከቤቷ የገባ ሰዉ ቤተሰቧ ነዉ የሚሆነዉ፡፡ አዲስ እንግዳም ሲመጣ አስተናጋጁ የሚጠሩላትም አይጠፋም ፡፡

“እንዴ ወ/ሮ አልማዝ …” ብዬ ሳልጨርስ “አይ ሶል ወ/ሮ ምንምን? ይኸን ማራቅህን ተዉ፡፡ እኔ አልሚ ….ኤልዬ….ዲያመንድ፤ አሳዋ ሲሉኝ እንጂ እንደ አልፎ ሂያጅ ወ/ሮ ቆይተህ ደግሞ እትየ …አይመቸኝም ይኸ ሶልዬ!” ብላ ፀጉሬን ድብስብስ እያደረገች ይኸዉ ልክ እነዚህ ለማኞች ስታያቸዉ ደሃ ነዉ የሚመስሉት ፈጣኖቹ በአዘቦት ቀን ከ250-300 ብር ደከም ያሉት ደግሞ ከ100-150 እያመጡ ይዘረዝሩናል፤ በክብረ በኣላት ደግሞ ከ450-500 ብር ሳንቲም ያመጡልናል፡፡

ከአንድ ብር ማዘርዘርያ ሃያሳንቲም ያስከፍሉናል፡፡ ከ500 ብር ስንት እንደሚያገኙ ይታይህ! ደግሞ ዛሬስ አለችና የዶላሩን እርግጠኝነት ባታጣዉም በጣም ተደንቃ እሺ በስንት ነዉ? እንስማማ? እያለች አንዴ ወደ ፍዝቀይ ቆቡ ባለቤት አንዴ ወደ እኛ እያማተረች ከወዲያ ወዲህ ግልብጥብጥ እያደረገች ማፈነጣጨዋን…. የባንኮኒዉን ኪስ መልሳ ዘጋችና ሳቅ አለች፡፡ ጓደኛዬ ስመኝዉ የቂጥና የጡት ነገር ላይ አይኑን ጣለ ማድረጉ የተለመደ ነዉ፡፡ አይ ስሜ! ይኸስ ለጉድ ነዉ! ብዬ እኔም ባይኔ ስከታተላት ፡፡

“እረ ምኑን ሰጠሽ?” ያለዉ አርቲስቱ ወዶ አይደለም በለሆስ ተናገርኩ ጓደኛየም ታእቦኝ ወደ ጀመርነዉ አለና ሀሳቤን መለሰዉ፡፡

ሌሎች እንግዶች እየተከታተሉ ገቡ፡፡ አስተናጋጆች ፈጥነዉ ደረሱላቸዉ፡፡ አልሚ “በል እንጂ ስራ አለብኝ እኮ አይዞህ እንስማማ ወደ ፊት የምንጠቃቀመዉ ይበልጣል::” አለችና እየሳቀች አግባባችዉ “አስራ ዘጠኝ ብር ሒሳብ” አላት፡፡ መልሳም “በቃ ስለምፈልገዉ አስራ ሰባት ከሃምሳ ላርገዉ?” ስትለዉ ፈጠን አለና “ባይሆን አሰራ ስምንት ያርጉት” “በል በል ስትፈልግ ነዉ፡፡ አለበዚያ ዉሰደዉ ፖሊስ ያገኝህ እንደሁ!” ስትለዉ “እሺ” አለና ና ስትለዉ ተከትሏት ወደ መኝታ ቤቷ ገባ፡፡ ዘረዘረችለትና “ግን ይኸን ወስደህ ምንድን ነዉ የምታደርገዉ?” ብላ ጠየቀችዉ እርሱም “እኔ አስናቀ ካገሬ ባለ 120 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት አለኝ፣ 2 የወተት ላሞችና 3 በሬዎች አሉኝ፡፡ ዘንድሮም ባለ አራት ቋት ወፍጮ የኳሳ ከተማ ላይ ተክያለሁ፡፡ የኳሳ ማለት ከዚያዉ ስማዳ ወረዳ ሁኖ አሁን መንገድም ተሰርቶለታል፡፡ ከተማዋም ለምታለች፡፡ 12 ገመድ መሬትም በአበል ገዝቼ እያረስኩ ነዉ፡፡ እረ ሃብታም ነኝ…..የኔም የራሴ አራት ገመድ መሬት አለኝ፡፡ ዘንድሮ ምርቱ አልሰጠም እንጂ….. ብቻ ደህና ነኝ! ምሽቴም ቡናና ጨዉ ነበር የምታገላብጠዉ አሁን እሷ ተዚያዉ የኮሳ ተወፍጨዉ ጎን ሱቅ ካልከፈተክ ብላኝ ወደዚያ ነዉ መንገድና አሳቤ” አለ፡፡

አልሚ በመደነቅ ሌላዉስ እንደዚ በየቀኑ የምትጋኘዉ? ብላ ጠየቀችው፡፡ “ሌላዉም ያዉ ከባንክ ነዉ ያለዉ፡፡ ዛሬ ላይ ፈርቼ አንዱን ጎን ከመንግስት አንዱን ጎን ከግል ባንክ ነዉ አግብቼዉ ያለ” አለና ፈገግ ብሎ ሁኔታዋን ለመረዳት ተመለከታት፡፡

“አስናቀ ከባንክ ስንት አለህ?” አለችዉ አልሚ ፈገግ፣ ፈገግ እያለች ውስጧ ድብን እንዳለ እንዳይታወቅባት በመሸፈን፡፡ “እረ ገና ነዉ አንድ ሰባት ድርሷል“ አለና ፍዝቀይ ቆቡን ወደ ግንባሩ ሳብሳብ እያደረገ … “ሊሄድ ነዉ ዛሬ መብል መሳይ የለም?“ ሲል እያፈረ ጠየቀ፡፡ የልመና ልማዱ አስቸግሮት

‘‘ልጆች … ነይማ ሮዛ፡፡ የዘንድሮ ሰራተኞች ወደ ከተማ ስትገቡ ሙጭት፣ ማሚት፣ አለማጫሽ …የምትባሉት ሁሉ ከወደ እስራኤል የመጣችሁ ይመስል ኤልዳና፣ ርሃዋ … ቤቴል እንደ ፈረንጅ ዉሻም…ሱቲ…ቲቲ… ቢቢ….መባል ትወዳላችሁ፡፡ ነይማ ሮዛ” እንዳለች አልማዝ “እመት አልሚቲ! ምን ልታዘዝሽ” … ብላ ሮዛ ቀረበች፡፡

“በይ ለዛሬ አንድ ሚስቶ አምጭለት፡፡ ሁለት ጃምቦ ድራፍትም ልጋብዘዉ፡፡ ቶሎ በይ” ብላ ፈገግ አለችና “ወደ ጨዋታችን እሺ ቅድም ሰባት ስትል አልገባኝም?” አለችዉ ፈራ ተባ እያለች፡፡ “ሰባት መቶ ሺ ነዉ፡፡ አንድ ሦስት መቶዎን በዚህ ሁለት አመት ቢጨምርልኝ (አንድ ሚሊዮን ብር) ከዚያ ካገሬ አርፌ እየነገድኩ ነዉ የምቀመጠዉ፡፡ የሰዉ አይኑ፣ ዉረፋዉ በዝቶብኛል፡፡ አንድ ልቤ አንድህ ሲል አንድ ልቤ ደግሞ ሁለት አመት ይዘኸዉ በዚሁ ብትቀጥልና ያለኝና አንድ የሚከራይ ደህና ግቢ ያለዉ ቤት ገዝቼ ልጆቼ የከተማዉ ነፋስና ስልጣኔ እንዲገባቸዉ ላምጣቸዉ እላለሁ …..ግን ወፍጮዉ ሲፈጭ በቀን እስተ ሺህ ብር የሚያስገባበት ጊዜ አለ እንደፋሲካ ከሆነማ ሙሉ ገቢዉም ዝቆሽ ነዉ” አላት እየተንከተከተ፡፡ “ባለቤቴ ግን ተዚኸዉ እንኑር ነዉ የምትለኝ፡፡ ሀሳቤን አልቆረጥኩም፡፡”

አልሚ “ለምን አንድ ሁለት …ሦስት መቶዉን በወለድ አታበድረኝምና ከኔ ጋር አብረን አንሰራም” አለችዉ፡፡ የእኔ ሰአት ስለደረሰ ስነሳ ስመኝዉም ሌላ ጉዳይ ኑሮት በትክሻ ተገጫጭተን ተለያየን - የዉሎ መሰንባበት አይነት ፡፡


ወደ ገጽ 12 ዞሯል

# የማላታየን ቅኝት ...

ከገጽ 11 የዞረ

### ሀ. ከርጭት በፊት የሚወሰድ ጥንቃቄ

- የተከሰተውን ተባይ አይነት፣ የጉዳትና መጠኑን ማወቅ
- ትክክለኛውንና በሚገባ የሚሰራ መርጫ መሳሪያ ማዘጋጀት




### ለ. በርጭት ወቅት የሚደረግ ጥንቃቄ

- አስፈላጊውን የመከላከያ ትጥቅ መልበስ --ጓንት፣ማስክ፣ መነፅር፣ ቦት፣ ቱታ ወዘተ
- ትክክለኛውን የመርጫ መሳሪያ መምረጥ
- የርምጃ ፍጥነትን፣ የነፋስ አቅጣጫና ፍጥነት ገምተን መርጨት



- በርጭት ወቅት አለመመገብ



- በኃይለኛ ፀሐይ ወይንም ከርጭት በኋላ በቶሎ ዝናብ የሚዘንብ መሆኑን ከገመትን አለመርጨት
- ርጭቱ ካልተፈለገ ቦታ እንዳይሄድ መጠንቀቅ

### ሐ. ከርጭት በኋላ የሚደረግ ጥንቃቄ

- የመርጫ መሳሪያውን በሚገባ ማጠብ
- ከርጭት በኋላ ሰውነትን በሚገባ መታጠብ
- ባዶ የፀረ-ተባይ መርዝ መያዣ እቃዎች ለተለያዩ የቤት ውስጥ አገልግሎት እንዳይሰጡ በስቶ ማስቀመጥ /መቅበር/
- ከተረጨ ማሣ ሰውና እንስሳት እንዳይገቡ ምልክት ማድረግ


## በፀረ-ተባይ ኬሚካል ክምችት ወቅት የሚደረጉ ጥንቃቄዎች

### ሀ. በፀረ-ተባይ መጋዝን መስሪያ ቦታ መረጣ ወቅት

- ከሰውና ከእንስሳት መኖሪያ ቢያንስ ከ30-100ሜትር
- ከውሃ ምንጭና ኩሬዎች ቢያንስ 200 ሜ/ር የራቀ ሊሆን ይገባል፣
- ለተሽከርካሪዎች መግቢያና መውጫ ምቹ መሆን አለበት::

### ለ. የማከማቻ መጋዝን ግንባታ ወቅት የሚደረግ ጥንቃቄ


- መጋዝኑ ነፋሻና ቀዝቃዛ እንዲሆን በቂ ክፍተት ያለበት መሆን ይኖርበታል



- መጋዝኑ ሁለት የተለያዩ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል፤ አንዱ ለማከማቻ ሁለተኛው ለቁሳቁሶችና መረጃ ሰነዶች እንዲሁም ለመታጠቢያ
- ከመታጠቢያዉ ክፍል ውሃና ሳሙና ቢኖር ይመረጣል
- ለፀረ-ተባይ መርጫ መሳሪያዎችና ኬሚካሎች ማስቀመጫ መደርደሪያ ሊኖረው ይገባል
- የመጋዝኑ በር በርሚሎችን ለማውረድና ለማስገባት ምቹ ሊሆን ይገባል::

### ሐ. በክምችት ወቅት የሚወሰድ ጥንቃቄ

- የመጋዝን ሠራተኛው በመጀመሪያ ስለ ፀረ-ተባይ ኬሚካል ምንነት፣ አያያዝና አጠቃቀም ስልጠና ያስፈልገዋል
- ፀረ-ተባዮች እንደአይነታቸው ተለይተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል::




ፀረ-ተባዮች እንደአመጣጣቸው ቅደም ተከተል ተለይተው ሊቀመጡ ይገባል፤

- አዲስ የመጡት ወደ ኋላ ተቀምጠው ወጭ ሲሆን ደግሞ ቀድሞ የመጣው መጀመሪያ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ይገባል::/First in first out/
- ፀረ-ተባዮች የመለያ ጽሑፋቸው እንዳይጠፋ መጠንቀቅ ፤ በየወቅቱም ማደስም ያስፈልጋል::
- በፀረ-ተባይ መጋዝን ውስጥ ለምግብነት የሚያገለግሉ እህሎች ወይንም ሌሎች የመገልገያ ቁሶች ፈጽሞ መቀመጥ የለባቸውም::
- እያንዳንዱ ፀረ-ተባይም ሆነ መርጫ መሳሪያ የራሱ የሆነ የነፍስወከፍ ካርድ ቁጥር(Bin card) ሊኖረው ይገባል::
- ለማንኛዉም ሰዉ በመጋዝን ውስጥ ለብዙ ጊዜ መቆየት የተከለከለ ነው::
- የመጋዝን ሠራተኛው በየጊዜው የሰውነቱን የኮሌስትሮል መጠን ለማወቅ የጤና ምርምራ ማድረግና ከፍ ብሎ ከተገኘም ወደሌላ የስራ መደብ መቀየር ያስፈልገዋል፤

### ፀረ-ተባይ ሲጓጓዝ መወሰድ ያሉባቸው ጥንቃቄዎች

- ፀረ-ተባዩ በሚጓጓዝበት ወቅት ሌሎች ለምግብነት የሚያገለግሉ ነገሮች አብረው መጫን የለባቸውም
    - በካርቱኖች ላይ ሌሎች ክብደት ያላቸዉን ነገሮች አለመደረብ
    - ፀረ-ተባይ ኬሚካል የሚያጓጉዝ መኪና በርሜልንም ሆነ ካርቶኖችን አካል የሚበሳ ነገር እንዳይኖር መጠንቀቅ ያስፈልጋል::

### በፀረ-ተባይ ኬሚካል መበከያ /መመረዣ/ መንገዶች


- ከኬሚካሉ ጋር በመነካካት (dermal contact)
- በእስትንፋስ አማካኝነት ወደ ውስጥ ሲገባ (inhalation)
- በድንገት በአፍ ቢዋጥ (oral ingestion)

### በፀረ-ተባይ ኬሚካል የመመረዝ ምልክቶች


- ማላብ፣ የምራቅ መብዛት፣ ፈሳሽ ከአፍና ከአፍንጫ መውጣት፣ የመተንፈስ ችግር ፣ መዝለፍለፍ፣ ማስቀመጥ፣ ወዘተ...

### በፀረ-ተባይ ኬሚካል ለተመረዘ ሰው መደረግ ያለበት የመጀመሪያ እርዳታ

- አንድ ሰዉ በፀረ-ተባይ መመረዙ ከተጠረጠረበት ስፍራ ራቅ አድርጌ በነፋሻ ቦታ ላይ ማስቀመጥ



- በሽተኛው እንዲቀዘቅዝ ልብሱን አውልቆ በውሃ ማጠብ




ወደ ገጽ 16 ዞሯል


# የማላታየን ቅኝት ...

ከገጽ 15 የዞረ


- ፀረ-ተባይ በአፍ የገባ ከሆነ እንዲያስመልስ ማድረግ



- የመተንፈስ ችግር ካጋጠመው በሰው ሰራሽ የማስተንፈስ ዘዴ እንዲተነፍስ ማድረግ



- ከዚያም የተመረዘበትን የኬሚካል አይነት መረጃ በመያዝ ወዲያውኑ ወደ ሐኪም ቤት መውሰድ



ማላታየን ኦርጋኖፎስፌትስ ተብለው ከሚታወቁ ጸረ-ተባዮች (insecticide) ኬሚካሎች አንዱ ሲሆን በተለምዶ ከማሳ ተባይ ለማስወገድ፣ የወባ ትንኝ ለመግደል፣ ከጸጉር ቅማል ለማስወገድ እና ለመሳሰሉት ስራዎች ይውላል::

ማላታየን ሰውነት ውስጥ የሚገባባቸው መንገዶች:-

➢ በትንፋሽ መልክ፣ በቆዳ ንክኪት ወይም በአፍ በኩል

ማላታየን ተባዮችን የሚገድልበት መንገድ:-


እንደ ጸረ-ተባይ ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ ወደ ተባዮች የነርቭ ሲስተም ይገባና አሲታይልኮሊንኢስተሬስ (Acetylcholinesterase (AChE)) የተባለውን ኢንዛይም ስራውን ሙሉ በሙሉ በማደናቀፍ አሲታይልኮሊን የተባለው ኒዩሮትራንስሚተር ከመጠን በላይ እንዲጨምር በማድረግ የነርቭ ሲስተም ከልክ በላይ ለረዥም ጊዜ በማነንንት (prolonged overstimulation) ተባዮች/ነፍሳቶች/ መንቀሳቀስ እንዳይችሉና ፓራላይዝድ እንዲሆኑ እንዲሁም በአግባቡ መተንፈስ እንዳይችሉ በማድረግ ይገድላቸዋል::

በአጠቃቀም ወቅት መደረግ ስላለባቸው ጥንቃቄች ለምሳሌ:-

- ለጸረ-ተባይ ከመጠቀማችን በፊት ስለአጠቃቀሙ ሙሉ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል:: ይኸውም ከባለሙያች ምክር፣ ማሸጊያው ላይ ከተፃፈው መመሪያ (label instructions) ማወቅ ይቻላል::
- በሚረጭበት ጊዜ የደንብ ልብስ መልበስ ያስፈልጋል::
- ተባዮችን ቶሎ ለመግደል ተብሎ ከመመሪያው ውጭ ከመጠን በላይ ማላታየን መጠቀም አያስፈልግም:-ለሰው ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል::
- ህጻናት እንዳያገኙት መጠንቀቅ ያስፈልጋል::

ጥንቃቄ የጎደለው አጠቃቀም ከሚያስከትላቸው ችግሮች ውስጥ:-

- ማላታየን ሰው ላይም ተመሳሳይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ሲሆን ጉዳቱ እንደየመጋለጥ መጠኑ ይለያያል:: (central nervous system overstimulation leading to depression, anxiety, headache, vomiting, skin and eye irritation, hyperactivity or restlessness, excessive sweating, shortness of breath, seizures, coma, and even death.)
- ማላታየን ዓሳ፣ ንብ እና አእዋፍ ላይም ከፍተኛ የጤና ችግር ያስከትላል::
- ለረዥም ጊዜ ለማላታየን መጋለጥ ለተለያዩ የንንሰር አይነቶች ሊያጋልጥ እንደሚችል አይጥ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ::
- ማላታየን ለእፅዋዕት ወይም የውሃ ወስጥ አልጌ መርዛማ አይደለም ምክንያቱም የስራው ዘዴ የሚያነጣጥረው የነርቭ ሲስተም ላይ ነው::



እኔም በመጨረሻ መደምደሚያውን ይህን ለምታነቡ አንባቢያን በተለይም በጥናትና ምርምሩ ዘርፍ ለምትሰሩ ትቼ በዚህች ግጥም ልሰናበታችሁ::

የሀገሬ ሰው አንተ የሀገሬ ሰው፣

ደምህ መስታወቴ ደሜ መስታወትህ የሆነው፣

የደምህ መጣራት ከጆሮዬ ገብቶ እንደው፣

እኔ ሰላም አላገኝ በዝምታስ አላልፈው፣

ደመ-ጩኸትህን ከሀገሬው ሰው ደም ሳላደርሰው::

# ውርስ ...

ከገጽ 6 የዞረ

መቼም በወጌ ውስጥ እንደተገነዘባችሁት የእኔ ቤተሰብ  የእድሜ ባለፀጋ ነው:: አንዳንዶች እንደሚሉት ከሆነ የእናንተ ቤተሰብ የዘር ሀረጉ ከማቱሳላ ሳይሆን አይቀርም ይሉናል፡፡ እኔ ግን በዚህ ሀሳብ አልስማማም ማቱሳላ ዘጠኝ መቶ ምናምን አመት ሲኖር ከመኖሩ ውጭ አዳች የሰራው ታሪክ አልተጠቀሰም፡፡ እህል እየበሉ መኖር ብቻ ከሞት የሚለይበት መተንፈሱ ብቻ ነው፡፡ እርግጥ ነው ታሪክ ሰርተንበት ካለፍን የእድሜ ባለፀጋ መሆን ደስ ያሰኛል፡፡ የማቱሳላ የእድሜ ጣሪያ በተጠቀሰበት መፅሐፍ ቅዱስ ላይ የኖህም እድሜ ልክ ተገልጧል:: ነገር ግን ኖህ “ኖሮ ሞተ” ከሚል ቃል ባሻገር ዛሬ እኔና አንባቢዎቼ በምድር ላይ እንድንኖር በእምነቱና በስራው ምክንያት ሆኖ ማለፉንም ይገልፃል፡፡ እንግዲህ እኔና የዘመኔ ትውልድ “ኖሩና ሞቱ” ከመባል የሚያወጣው ትልቅ አጋጣሚ ስለተፈጠረ ያስደስተኛል፡፡ ቅድመ አያቴ በቁጭት ሲያንጐራጉርበት ያቅሙን አድርጐ በተስፋ የአባይን ወንዝ ውሃ ተጐንጭቶ ቢያልፍም ቁጭቱን ተወጥቶለት መንፈሱን የሚያሳርፍበት ትውልድ ዛሬ አግኝቷል፡፡

በበኩሌ ወደፊት ሳረጅ አፌን ሞልቼ ለልጅ ልጆቼ የምናገረው ታሪክ አለኝ:: ዛሬ ላይ ሆኝ የእርጅና ዘመን ልምላሜዬን... በተስፋ እየዋለሁ... ተስፋው እውን እደሚሆን እርግጠኛ ነኝ፡፡ ልጆች ዙሪያዬን ከበው “ትልቁ አባባ ተረተ አውራልን...” ሲሉኝ ልጆቼ እኔ ተረት ሳይሆን ያኔ በእኛ ዘመን የተሰራውን ታሪክ ነው የምነግራችሁ ስላቸው” ትልቁ አባባ እስቲ ዘፈን ዝፈንልን? ሲሉኝ ደግሞ

አባይ ወርዶ ወረዶ ይገባል ህዳሴ

እንግዲህ ብሞትም አትቆጭም ነፍሴ

ቁጭቱ ተረስቶ ታሪክ ተቀይሯል

አባይ የፍቅር ወንዝ ኢትዮጵያን ያጠግባል...

እያልኩ በደስታ... አንጐራጉርላቸዋለሁ፡፡ እንግዲህ አንባቢዎቼ የእኔና የቅድመ አያቴ ውርስ ልዩነቱና አንድነቱ ይህን ይመስላል፡፡ ለኢትዮጵያ ሲል አባይ ወንዝን የፈጠረ አምላክ ይባርካችሁ 8100Aን ያሳስባችሁ... ሰላም!

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

ላለፉት ሶስት ወራት በተለያዩ ምክንያቶች ጋዜጣችችን ለአንባቢያን ባለማድረሳችን አንባቢዎቻችንን ይቅርታ እየጠየቅን ጋዜጣችንን የበለጠ ተደራሽ እና ተነባቢ ለማድረግ እየሰራን እንገኛለን፡፡ እርስዎም በጋዜጣችን ላይ በመሳተፍ በመማር ማስተማር፣ በምርምር፣ በማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሁም በቴክኖሎጂ ሽግግር የተገኙ እውቀት፣ ሀሳቦችን፣ አስተያቶችን እንዲሁም አመለካከቶችን በማንሳት ማህበረሰቡ እንዲማርበት፣ እንዲወያይበትና እንዲከራከርበት በማድረግ ሃላፊነትዎን ይወጡ!

ዝግጅት ክፍሉ

ጎህ ማተሚያ ቤት ታተመ